# የተባረከው ተስፋችን

## ሚሌኒየም ዘኢትዮጲስ

ከግርማ ዘውዴ አንጁሎ

፪ ሺህ / 2000 ዓ.ም

ክፍል አስራ አምስት
ሦስቱ የሚሌኒየም አመለካከቶች
15.1 አልቦ ሺህ ዓመት ውስጥ ነን (Amillennialism) . . . 67
15.2 ድህረ ሺህ ዓመት (postmillennialism). . . 69
15.3 ቅድመ ሺህ ዓመት መንግሥት (premillennialism) . . . 71
ክፍል አስራ ስድስት
የታላቁ መከራ አመለካከቶች
16.1 ከቅድመ ሺህ ዓመት መንግሥት በፊት የሚሆነው ታላቅ መከራ . . . 73
16.2 እስራኤል በታላቁ መከራ ወቅት . . . 74
ክፍል አስራ ሰባት
ስለ ሺህ ዓመት የተሰጡ ትርጉሞች
17.1 በአልቦ ሺህ ዓመት መንግ/ ት ውስጥ ነን የሚሉ (AMillennialism) ሰዎች የሚሰጡት ትርጉም . . . 76
17.2 ስለ አመለካከት ልዩነት . . . 76
17.3 የሰይጣን ጉልበት መሰበርና መታሰሩ. . . 77
17.4 የተለየ የሙታን ትንሳኤ አመለካከ . . . 79
17.5 የቅድመ ሺህ ዓመት አማኞች ምላሽ . . . 80
17.6 ሺህ ዓመት ውስጥ ነን የሚሉ (AMillennialists) አመለካከት. . . 82
17.7 የሙታን መነሳት እና የሺህ ዓመት መንግሥት በሌላ አመለካከት . . . 83
ክፍል አስራ ስምንት
ፊተኛው ትንሳኤ
18.1 ስለ ትንሳኤ የዮሐንስ ራዕይ ግልፅ ማብራሪያ . . . 85
18.2 ኑሮ በሺህ ዓመት መንግሥት ውስጥ . . . 86
18.3 የሺህ ዓመት መንግሥት ውበትና ድንቅ ውጤት . . . 87
18.4 የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለህዝቡ . . . 88
ክፍል አስራ ዘጠኝ
የድህረ ሺህ ዓመት አስተሳሰብ
19.1 የድህረ ሺህ ዓመት መንግሥት (postmillennials) የመከራከሪያ ሀሳቦች . . . 90
19.2 የድህረ ሺህ ዓመት መንግሥት (postmillennials) አስተሳሰብ . . . 92
ክፍል ሃያ
መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ ስለ ሺህ ዓመት መንግሥት (Millennium) . . . 95
የራዕይ ዋና ዋና ክስተቶች - ቻርት . . . 98
ክፍል ሃያ አንድ
ቅድመ ሺህ ዓመት መንግሥት (Premillennium) ከሌሎች የሚለይባቸው ባህሪያት
21.1 የዘመኑ ልዩ መሆንና የትኩረት አቅጣጫ . . . 99
21.2 ነቢዩ ዘካርያስ ስለ ሺህ ዓመት ያየው ራዕይ ሲተነተን . . . 102
21.3 ስለ ትንሳኤ የጳውሎስ ትምህርትና ትንታኔው . . . 103
21.4 ለአውሬው አለመስገድና ከክርስቶስ ጋር መንገሥ . . . 105
ክፍል ሃያ ሁለት
ታላቁ መከራ
22.1 የቤተክርስቲያን መነጠቅ . . . 107
22.2 አንደኛውና ሁለተኛው «የሦስት ዓመት ተኩል» ጊዜ . . . 110
22.3 የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ጉዞ . . . 111
ክፍል ሃያ ሦስት
የመጨረሻው ፍርድና የዘላለም ቅጣት
23.1 የተከፈቱ መጻሕፍትና ሌላው መጽሐፍ . . . 113
23.2 የዲያብሎስ ለጥቂት ጊዜ መፈታት . . . 113
23.3 የሙታን ትንሳዔ ወቅት . . . 114
ክፍል ሃያ አራት
የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ
24.1 የፍርዱ አሰጣጥ . . . 116

## ክፍል ሦስት

# ሀሳበ ዘመን በኢትዮጵያ

### የኢትዮጵያ የሀሳብ ዘመን አመጣጥ

በኢትዮጵያ የዘመናት፣ የአመታት፣ የወራት፣ የሳምንታት፣ የዕለታት፣ የሰዓታትና የደቂቃ ጊዜያቶች አቆጣጠር የተዘጋጀው በግብፃዊው ዮሐንስ አቡሻክር እንደሆነ ይታወቃል። ይህም የሀሳብ ዘመን አቀራረብ በኢትዮጵያ ሊቃውንት ዘንድ ዝነኛና የተወደደ ሆኖ በመገኘቱ ተቀባይነት አግኝቶ ቀመሩ በዚሁ በተጠቀሰው ሰው ስም ተሰይሟል።

ይህም የተዘጋጀበት ዘመን ከ1240-1250 ዓ.ም ባሰው ጊዜ እንደሆነ በአለቃ መሰረት ስብሐተ ለአብ የተዘጋጀ ‹‹ሀሳብ ዘመንና ታሪኩ›› የተሰኘ መጽሐፍ ሲያስረዳ በሰንከስር ላይም ተገልጾአል። ከነዚህም በተጨማሪ ከ200-240 ዓ.ም ገደማ የነበረው የእስክንድሪያው (የግብጹ) ጳጳስ ዲሜጥሮስ በዓላትና አፅዋማትን ለመወሰንና ጊዜያቸውንም ለማስተካከል እንዲሁም የቁጥር ሕግ ለመስጠት ተመኝቶ ሱባኤ ገብቶ ይኸው የተጠቀሰው የዘመን ቀመር ተገልጦለት ነበር የሚል አፈታሪክም አለ። በአጠቃላይ ግን የኢትዮጵያ ሀሳበ ዘመን አመጣጥ ከፋርስ፣ ከእስራኤልና ከእስክንድሪያ (ከግብጽ) እንደሆነ ይገመታል።

የዕለታትን አቆጣጠር በተመለከተ ዐውደ ዕለታት የሚባሉት ከእሁድ እስከ ቅዳሜ ያሉትን ሰባት ዕለታት አውራኀንን (ወሮችን) ለማስገኘት በዚህ አቋም ሲመላለሱ ይኖራሉ። እነዚህም ሰባት ዕለታት ከጥንተ ሥነ-ፍጥረት ታሪክ





ጀምሮ በዚሁ ስምና መደብ ቀመር ተሰጥቶአቸዋል። ዐውደ ወርኅ (ወር) ዘወትር ሠላሳ ሠላሳ እየሆኑ በጨረቃ ግን አንድ ጊዜ ሠላሳ ሁለተኛ ጊዜ ሀያ ዘጠኝ በመሆን እየተፈራረቁ ዓመታትን ለማስገኘት በዚሁ አቋም ሲመላለሱ የሚገኙበት ነው።

ዐውደ ዓመት የሚባለው በፀሐያዊ ቀን አቆጣጠር 365¼ በጨረቃ ደግሞ 354 ቀን እየሆኑ የዓመትን ሙሉ ዑደት (ዙር) የሚያስገኝ ነው። በዚሁ መሰረት ቀመሩ በፀሐያዊ ዕለት በሠላሳ በሠላሳ ተከፍሎ አስራ ሁለት ወራት ሲሆን ተጨማሪ አምስት ቀን ከሩብ የሆነውና አጭሩ ወር ጳጉሜን ይታከልበታል። ይህ አቀማመር በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት ሆኖ አንዳንድ ጊዜ ዓመተ-ኖህ በሚል ዘይቤ የሚታወቅ የኢትዮጵያና የግብፅ (የምስር) ጥንታዊ የዘመን አቆጣጠር ባህል እንደሆነ ግልፅ ነው።

የዓመቱ ዐውደ ዕለታት ሃምሳ ሁለት ናቸው። ይህም የሚያመለክተው በመጀመሪያ ደረጃ ከላይ እንደተጠቀሰው የሳምንቱ ዕለታት ሰባት እንደመሆናቸው መጠን በአንድ ዓመት ውስጥ ሃምሳ ሁለት ጊዜ እየተመላለሱ ስለሚገኙ ሃምሳ ሁለት ሱባኤ ዕለታት ይባላሉ።

## ክፍል አራት

# የወቅቶች ቀመር

### የዓመቱ አራት ወቅቶች በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ አንዱ ዓመት በአራት ወቅቶች ተከፍሎ ይገኛል። ይኸውም፡

1ኛ) ከመስከረም 26 እስከ ታህሳስ 25 ዘመነ መፀው (ጥቢ) ሆኖ 91 ቀን ይይዛል።
2ኛ) ከታህሳስ 26 እስከ መጋቢት 25 ዘመነ ሀጋይ (በጋ) ሆኖ 91 ቀን ይይዛል።
3ኛ) ከመጋቢት 26 እስከ ሰኔ 25 ዘመነ ፀደይ (በልግ) ሆኖ 91 ቀን ይይዛል።
4ኛ) ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ዘመነ ክረምት ሆኖ 91 ቀን ይይዛል።

ይሁን እንጂ የአራቱ ወቅቶች እኩል 91ቀንX4= 364 እንጂ 365¼ ስለማይሞላ እና ስለሚፋለስ እና ሊቃውንቱ ሲቀምሩ የጎደለውን 30 ሰዓት (አንድ ቀን ከሩብ) በአራቱ ወቅቶች ባሉት ዘጠና አንድ ዘጠና አንድ ቀናት ላይ በእያንዳንዳቸው ሰባት ሰዓት ተኩል (7፡30) ይደምሩባቸውና እኩል 365¼ ቀን በመሆን ፍፁም ዐውደ ዓመት እንዲያስገኝ አድርገው ሠርተውታል።

በየዓመቱ የዕለት ሩብ ማለትም ስድስት ሰዓት ደግሞ በአራት ዓመት 6X4= 24 ሰዓት አንድ ቀን እንዲሆን ያደርገውና የአራተኛው ዓመት ቀኖች 366 ¼ ይሆናሉ ማለት ነው።





ወቅቶቹ መፋለስ እንዳያጋጥማቸውም ርዕሰ ዐውደ ዓመቱ የሚውልባቸው ቀኖች ይቆጣጠርላቸዋል። በተጨማሪም የአራቱም ወቅቶች (የጥቢ፣ የበጋ፣ የበልግ እና የክረምት) የአየር ፀባይ ከተመደቡባቸው ወራት እንዳይፋለሱ ይጠበቃሉ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም መወለድና ለሰው ልጆች የኃጢአት ዕዳ ለመክፈል በመስቀል ላይ በመሞቱ ነው። ስለሆነም የዘመኑ ቀመር እንደ ሊቃውንቱ አስተሳሰብ በዮሐንስ መጥምቁ ልደት መቀመሩ በዘመን አቆጣጠር ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ እውነታ ላይ ጥያቄ መፍጠሩ አይቀሬ ቢሆንም እስካሁን ያለው የዘመን አቆጣጠር እና ቀመሩ የሚሠራበት በዚሁ ሁኔታ ነው። ለወደፊቱ ግን ትኩረት ተሰጥቶ ጥናት ቢደረግ ክፋት የለውም።





## ክፍል ስድስት

# ቋንቋ፣ፊደልና ሥነ ጽሁፍ በኢትዮጵያ

### 6.1 የግዕዝ ፊደልና ቋንቋ መሠረቱ

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ያላት አገር ለመሆንዋ ከፍ ብሎ በዝርዝር ተገልጾአል። የጥንት ቅርሳ ቅርስ ሊቃውንት እና ታሪክ ጸሐፊዎችም እንዳረጋገጡት በኢትዮጵያ ፊደልና ሥነ ጽሁፍ የተጀመረው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺህ ዓመት ቀደም ብሎ ነው ይባላል። ነገር ግን የጽሑፉ መሠረት የሆነው ፊደል የተቀነባበረው እና በጽሑፍ ስልት በደንብ የታወቀው ደግሞ የክርስትና እምነት ወደ ሀገሪቱ ከገባ በኋላ ነው፤ በዚህም መነሻ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት በፊት የነበሩት የሳባውያንና የአግዓዝያን ፊደላት በጥምር ይሠራባቸው እንደነበር ታውቋል።

በዘመነ አክሱም ግን የግዕዝ (የአግዓዝያን) ፊደልና ቋንቋ እያደገ እንደመጣ እና ክርስቲያን ነገሥታትም በሀውልቶችና በዘመናቸው በተቀረፁ የመገበያያ ሳንቲሞች ላይ በግዕዝ ፊደልና ቋንቋ ተፅፎባቸዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከሚጠቀምባቸው ልዩ ልዩ የታሪክ የሕግ የግጥም የሰዋሰው የፍልስፍናና የመድሃኒት ቅመማ ወዘተ... መጻህፍት የተጻፉትና የተዘጋጁት በሳባ (በግዕዝ) ፊደል ነው።

## 6.2 የቋንቋ ታሪካዊነት ለሥነ ፅሁፍ

ለማንኛውም ጽሑፍና ቋንቋ መሠረቱና መነሻው ፊደል መሆኑ የታወቀ ነው። አንድ ቋንቋ ታሪካዊ ቋንቋ ነው የሚባለውም ፊደል ቀቀርፆለት የሥነ ፅሁፍ መሠረት ሲሆንና መልዕክቱን በሥነ ፅሑፍ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ሲችል ነው።

ስለሆነም ኢትዮጵያ የራሳቸውን ፊደል ካላቸው ጥቂት ጥንታዊያን አገሮች መካከል አንዷ ስትሆን ይህም ፊደል ባአገሪቱ ቋንቋ መቀረፁ ታሪኩን መዝግቦ ለማስቀመጥ እና በቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜም ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል።

ብዙ የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚስማሙበት በየመን (በዛፍር) የሰፈሩት የመጀመሪያዎቹ ሳባውያን "ሳባ" የሚል መንግሥት መሥርተው ለሴማዊ ቋንቋቸው ሳባዊ ፊደል ቀርፀው ሥልጣኔያቸውን ማስፋፋት እንደጀመሩ ታውቋል፡፡ እነዚህ ሴማውያን ወደ አሁኗ ኢትዮጵያ ሲገቡና በአገሪቱ ከነበሩት የጥንት ነዋሪዎች ከሆኑት ኩሻውያን ጋር የተቀላቀሉት ይህንኑ ሥልጣኔ ይዘው በመምጣት ነው።

ሳባዊ ፊደል የግዕዝ መነሻ ሆኖ ከዕብራይስጥና ከዐረብ ፊደላት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሲሆን ቋንቋው ከጥንቱ ሳባዊ ቋንቋ ተሻሽሎና ግዕዝ ከሚባለው ከመጀመሪያው ፊደል እስከ ሳብዕ ሰባተኛው ሆሄ ታድሶ የተቀነባበረ ነው። ይህም የግዕዝ ቋንቋ ከኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ጋር አብሮ በቀል ነው ለማለት ይቻላል።

የኢትጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የተለያዩ ባህል የአምልኮ ሥርዓትና የአኗኗር ሁኔታ ያላቸው ሲሆን እስካሁን ድረስ ለትላልቅ ወንዞች ተራሮች የሚሰግዱ ሰዎች ያሉባት አገር ናት። በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ለቃልቻ ለውቃቢና ለዛር የሚሰግዱ ለሰይጣን የተለያየ መስዋዕት የሚያቀርቡ ሰዎችም





እንዳሉ የታወቀ ነው። ሌሎች ደግሞ በየተራራው ላይ ለተሠሩት ጣዖታት እያማተቡ የሚሰግዱ ድንጋይ የሚሳለሙ ባዕድ አምልኮ የሚካሄዱ ብዙዎች ናቸው።

በተጨማሪም በየጠረፉ ያሉ ዜጎች የአለባበስ የአበላልና የማህበራዊ ኑሮ ሁኔታዎቻቸው ከሌሎች አካባቢዎች ጨርሶ የተለየ ነው። ይህንን ሁሉ በመረዳት ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ትክክለኛ አምልኮ የሚመለስበትን በማቀናጀት ለመሥራት ከሚሊኒየሙ ዓላማዎች አንዱ ሆኖ ቃል በተግባር የሚተረጎምበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት።

ከዚሁ ጎን ለጎን መልካም ባህላችንን እያበላሸና እየመረዘ ያለው ደግሞ ከላይ ጀምሮ እስከታች ድረስ ያለው የርስ በርስ ምቀኝነትና ቅንዓት ነው። የጓደኛው የጎረቤቱ ወይም የወንድሙ እልፍ ማለት እንቅልፍ የሚያሳጣው በርካታ ሕዝብ ስለሆነ እግዚአብሔር ይህንን እርግማን እንዲያስወግድና አንዱ የሌላውን እድገት ለመግታትና ለማጥፋት ከመሯሯጥ ይልቅ የራሱን ሥራ ሠርቶ መኖር የሚችልበትን መንገድ መፈለግ አለበት።

ሌላው ደግሞ የጦረኝነትና የጀብደኝነት ስሜት ተውግዶ በሥራ ፈትነት ሳይሆን በሠራተኛና በትህትና እግዚአብሔርንም በመፍራት ለመኖር መዘጋጀት ቢቻል ሀገሪቱ ከወደቀችበት የድህነት አዘቅት በቶሉ ልትወጣ እንደምትችል የታመነ ነው። በሀገራችን ከስም አወጣጥ ጀምሮ እስከ ቃልና ተግባር ድረስ ያለው ሁኔታ አንዱ ከሌላው የበላይ ለመሆን የሚያደርገው የሥጋዊ ቅንዓትና ውድድር መሆኑን ያሳያል።

ከዚህም የተነሳ በሰላማዊ መንገድ ሊያልቁ የሚገባቸው የእርስ በርስም ሆነ የውጪ ግጭቶች የጦርነት አማራጭ ብቻ እየተወሰደባቸው ለሀገር ልማትና ለህዝበ እድገት ሊውል የሚገባው የሰው ሀይልና መዋዕለ ንዋይ በከንቱ ወድሞ ሀገሪቱ ዛሬ የደረሰችበት ደረጃ ላይ እንድትገኝ ምክንያት ሆኗል።

ስለዚህ መንግሥት ቃሉን አክብሮ የህዝቡ ረሃብ ረሃቡ ችግሩንም ችግሩ አድርጎ በቅንነት ያለአድልዖ ከሠራና ቃሉ በተግባር ከተተረጎመ እንዲሁም ህዝቡ ልቡንና መንፈሱን ለእግዚአብሔር አስገዝቶ ለሃገር ልማትና ለህዝብ እድገት ጠንክሮ ቢሰራ የታለመለትን የረሃብንና ድህነትን ታሪክ ሆነው እንዲቀሩ ለማድረግና ኢትዮጵያንም እንደሚባለው በ20 እና በ30 ዓመት ሳይሆን በቅርብ ጊዜ ውስጥ በዓለም ላይ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ እንድትገባ ማድረግ ይቻላል።





## ክፍል ሰባት

# የኢትዮጵያ ጥንታዊ ገንዘቦች አቀራረፅ

### 7.1 የመገበያያ ገንዘብ አሠራርና ዓርማው

ስለ ኢትዮጵያ የጥንት ሥልጣኔ ስንመለከት ልናውቀው የሚገባን አንዱ ጉዳይ በሀገሪቱ የነበሩትን የመገበያያ ሳንቲሞች አሠራርና አጠቃቀም ነው።

የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን አማካይነት በ330 ዓ.ም ገደማ እንደሆነ ይታወቃል። የኢትዮጵያ የመግበያያ ገንዘብ ደግሞ ከዚያም በፊት ተሠርቶ በሥራ ላይ ለመዋሉ የታሪክ ማስረጃ አረጋግጧል።

ከክርስትና በፊት በነበሩት ሳንቲሞች አናት ላይ የጥንት ሳባውያን የጣኦት አምልኮ ምልክት የሆነው ጨረቃና ኮከብ እንደ አርማ ተቀርፆ ሲገኝ ዛሬም አንዳንድ የእምነት ክፍሎች ይህንኑ የጨረቃና የኮከብ ምልክት እንደ መለያ አርማ ይጠቀሙበታል። የክርስትና እምነት ወደ ሀገሪቱ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በነገሡትና የክርስትናን ሃይማኖት በተቀበሉት ነገሥታት ዘመን በተሠሩ ሳንቲሞች አናትና መካከል ላይ የመስቀል ምልክት ተደርጎ የተቀረፀባቸው ሳንቲሞች ዛሬም በየሙዚየሙ ለአብነት ተቀምጠው ምስክርነታቸውን በመስጠት ላይ ይገኛሉ።







ክርስትና ከመግባቱ በፊት የተሠራው የንጉሥ ዔዛና የወርቅ ገንዘብ



ክርስትና ከገባ በኋላ መስቀል የተቀረፀበት የዔዛና የወርቅ ገንዘብ

## 7.2 የሥልጣኔው መውደቅ

የኢትዮጵያ ሥልጣኔ በተለይም ገንዘብን የመሥራት ጥበብ ከእስልምና መግባት፣ ከተለያየ የድንበር ግጭትና ከዮዲት (ጉዲት) ወረራ በኋላ ተንኮታኩቶ ሲወድቅ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ ለአንድ ሺህ ዓመታት ገደማ በኢትዮጵያ የመገበያያ ሳንቲም የማሠራቱ ጥበብና ሌላም ሥልጣኔ ጠፍቷል። ህዝቡ ለመገበያያ ይጠቀም የነበረው ዕቃ ከዕቃ ጋር በመለዋወጥ በአሞሌ ጨው፣ በጨርቃ ጨርቅ በብረት ቁርጥራጮች በብይዎችና በዛጎሎች እንደነበረ ይታወሳል።

የ18ኛው ክፍለ ዘመን እንግሊዛዊ ታሪክ ጸሐፊ አድዋርድ ጊቦን የሮም መንግሥት ውድቀት (The decline and fall of the Roman Empire) በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፉ ስለ ኢትዮጵያ (አክሱም) ሥልጣኔ መውደቅና መንኮታኮት ጠቅሶአል፤ በክፍሉም «ኢትዮጵያ በእስላሞች ተከብባ የጥንት የባህር በሮችዋን ከተነጠቀች በኃላ በሁሉም አቅጣጫ የሃይመኖት ጠላቶችዋ ክፉኛ ስለ ከበቡአት ኢትዮጵያውያን ዓለምን ረስተው ዓለምም እነርሱን ረስታ ለአንድ ሺህ ዓመት እንቅላፉ›› ብሏል።





ከዚህም በኃላ በዳግማዊ ምኒሊክ ዘመን የመገበያያ ሳንቲሞች የመሥራት ልምድ እንደገና ማገገም ጀመረ እንጂ የኢትዮጵያ የጥንት ሥልጣኔ በሚያሳዝን ሁኔታ ከፍተኛ ውድቀት ደርሶበታል። ጥንት ከሌሎች ከሠለጠኑ ሀገሮች ተርታ የነበረች ኢትዮጵያም የመጨረሻዋ ኋላ ቀር ሆና መገኘቷ እጅግ የሚያሳፍር ነገር ነው።

## 7.3 የወረቀት ብሮች እና የፍራንኮች መሠራት

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት አገሪቱ በሥልጣኔ ብዙ ባትገፋም የመገበያያ ሳንቲሞችና የወረቀት ብሮች ተሠርተዋል። እነርሱም የአንድ፣ የአምስት፣ የአስር፣ የሃያ አምስትና የአምሳ ሳንቲም ፍንኮች (coins) ተቀርጸዋል። የወረቀት ብሮችም የአንድ፣ የአምስት፣ የአስር፣ የሃያ፣ የአምሳ እና የመቶ ብር ኖቶች ተሠርተዋል። እነርሱም ከዚህ በታች የሚታዩት ናቸው።



ሃያ አምስት ሳንቲም

ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰላምታ መጽሔት

የተባረከው ተስፋችን











A735995
ONE HUNDRED
ETHIOPIAN DOLLARS
100
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
B291184
FIFTY ETHIOPIAN DOLLARS
50
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
TEN ETHIOPIAN DOLLARS
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA






100
10

በወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዘመን 1969 ዓ.ም ግን በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የተሰሩት የወረቀት ብሮችም ሆኑ የመዳብ ሳንቲሞች በሙሉ ተቀይረዋል።

ኢህአዲግ የደርግን መንግሥት ገልብጦ ኢትዮጵያን መምራት ከጀመረበት ከግንቦት 20/1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1989 ዓ.ም ድረስ ቀደም ሲል በነበረው መንግሥት በተሠሩት ገንዘቦች ሲሰራበት ቆይቶ የወረቀት ብሮቹ ላይ ለውጥ ሲደረግባቸው ፍራንኮቹ ግን ይህ ጽሑፍ እስከተዘጋጀበት ወቅት ድረስ እየተሠራበት ይገኛል።

በደርግ ዘመን የተሠሩት ዝርዝር ሳንቲሞችና የወረቀት ብሮች ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው፡ -









## ክፍል አስር

# የመጨረሻው ዘመን አሳቾች

## 10.1 ሐሰተኞች ነቢያት እና ሐሰተኛ ክርስቶስ

*‹‹በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ›› 2ጢሞ.3:12* ተብሎ እንደተጻፈ ይህንን የሐሰት ትንቢት ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ስለሆነ የማይቀበሉ ህይወታቸውን መስዋዕት አድርገው እንዳሳለፉ ታውቋአል።

*‹‹አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና›› ገላ.6:7*

ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተረጋገጠውን የግል መላምት ለህዝብ ማስተማር በእግዚአብሔር ዘንድ ኃጢአት ሲሆን በሕግ ፊትም ወንጀል ነው። ምክንያቱም ስለመጨረሻው የዓለም ፍፃሜ ከተነገሩት ምልክቶች በስተቀር እግዚአብሔር የወሰነውን ቀን ማንም ሊያውቅ አልተፈቀደለትም። በእርግጥ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የሚፈጸሙ ተአምሮችና የሚደረጉ ትርምሶች የዓለምን መጨረሻና የእውነተኛውን ሚሊኒየም መቃረብ የሚያመለክቱ ናቸው።

የአሁኑን ዘመን በኢየሱስ አገላለጥ ስንቃኝ *በማቴ.24:4-14* ብቻ የዚህን ዘመን ዘጠኝ ዋና ዋና ባህርያት ተናግሯል።

እነርሱም: -

1. ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚሉ ይመጣሉ እነዚህ ሐሰተኞችና አስመሳዮች ናቸው
2. ጦርነትና የጦርነት ወሬዎች





3. ረሃብ
4. ቸነፈር
5. የምድር መናወጥ
6. የብዙዎች ሰማዕት መሆን
7. ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉ
8. ከአመፅ ብዛት የተነሳ ብዙ ሰዎች ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር ይቀዘቅዛል
9. የእግዚአብሔር መንግሥት የምስራች (ወንጌል) በዓለም ሁሉ ይሰበካል። ያለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት የዚህን ትንቢት ትክክለኛነት መስክረዋል

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንመለከተው በብዙ ሀገሮች በአካል እኔ ክርስቶስ ነኝ ብለው ብዙ ሐሰተኞች ተነስተዋል። ነገር ግን የግድ በራሳቸው ስሜት ክርስቶስን ሊሆኑ ስለፈለጉ ብቻ መሆን ስለማይችሉ እንደጉም በነነው ጠፍተዋል።

## 10.2 በዚህ ዘመን ያሉ ሐሰተኞች ነቢያትና የቀበሮ

### ባህታውያን

በተለያዩ ዘመናት ሐሰተኞች ነቢያት መነሳታቸውና መጥፋታቸው የሚታወቅ ነው። እነርሱም ባላመኑት ሰዎች ዘንድ ሳይሆን በብዛት ያሉት የክርስትናን ሃይማኖትና መጽሐፍ ቅዱስን እንደጭምብል አጥልቀው የሚያሚርቱ ናቸው። እነዚህ ሰዎች መካከል በጥልቁ አሠራርና በሉሲፈር የሚንቀሳቀሱ ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ በስጋቸው ስሜት እና በሚርተኝነት በመገፋፋት ትንቢት እንናገራለን የሚሉ በቤተክርስቲያን ስር ሆነው መመሪያና ትምህርት ማይቀበሉና የማይሰሙ ናቸው።

*«...የአምልኮ መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል ከእነዚህ እራቅ...»* *2ጢሞ.3:5* የተባለላቸውና መጽሐፍ ቅዱስን ከቦታ ቦታ ይዘው የሚዘዋወሩ ናቸው። በእነርሱ የሐሰት ትንቢትና አሰራር ምክንያት እውነተኞቹና ከእግዚአብሔር ሰምተው ትክክለኛውን የትንቢት ቃልና መልእክት የሚያስተላልፉ እንኳን ጥያቄ ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል።

*«በዚህን ጊዜ ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ ሐሰተኛ ክርስቶሶች እና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሳሉና ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳን እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ» ማቴ.24:23-24፤* ይሁን እንጂ የመጨረሻው ምክንያቶች እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለምና በጥንቃቄ መመላለስና ማጤን አስፈላጊ ይሆናል።

ሌሎች አስመሳዮች ደግሞ ደሃውን ህዝብ ከቦታ ቦታ የሚያንከራትቱ እገሌ የሚባል ጠበል ፈልቋል የጠጣ ይፈወሳል፣ ሽባ እናድናለን፣ እውር እናበራለን፣ ደንቆሮ እናሰማን እያሉ አመድ እና ጭቃ እየቀቡ የሚመልሱ ናቸው።

እነርሱም በቅዱሳንና በሰማእታት ስም የሚያጭበረብሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ውጪ በሆነ በራሳቸው ወይም በሰይጣን ምሪት ሕብረተሰቡን የሚያሰቃዩ ናቸው። እነዚህ ከሐሰተኞች ተራ የሚመደቡ ሲሆኑ ፈውስን የሚጓጓ በሽተኛ ወይም የበሽተኛ ቤተሰብ በብርድና በርሀብ እንዲሁም በተላላፊ በሽታ እንዲያልቅ እያደረጉት ነው። ለነገሩማ እነርሱን ሐሰተኞች ወይም መናፍቃን ናቸው የሚል ሰው ለጊዜው ባይኖርም በቅርብ ቀን ግን ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆኑት ሁሉ ከሐሰት አሰራራቸው ጋር እርቃናቸውን እንደሚቀሩ አይጠረጠርም።

የእነዚህና የተመሳሳይ ሟርተኞች የጥንቆላ የመተት የድግምት የመጽሐፍ ገላጭነት የአስማት ሥራና ርኩሰት መናፍስትን መጥራት በክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይገለበጣል። ኢትዮጵያም እግዚአብሔር በገባላት የተስፋ ቃል





መሠረት የዘንዶ እራስ ሲቀጠቀጥ የተትረፈረፈ ምግብ ታገኛለች፤ ህዝቡም ይባረካል። *መዝ.74:14*

ሌሎች ሐሰተኞች ደግሞ በስልጣናቸውና በጡንቻቸው መፈርጠም የሚተማመኑ የእግዚአብሔርን ቃልና እግዚአብሔርን ራሱን የማያውቁ ናቸው። እነዚህ ደግሞ ሀይማኖተኞች ሆነው የሀይማኖቱን ደንብና ስርዓት የማይጠብቁ ናቸው *ማቴ.23:24፤* እነዚህ በተለይም እውነተኛውንና ትክክለኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ሙሉ በሙሉ ተቀብለው በማምለክና በማገልገል ላይ ለሚገኙት እንኳን የተለያየ ስም በመስጠት የሚያሳድዱ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ከተነበበና ሕብረተሰቡ መንፈሳዊውን ነገር በጥልቀት ከተረዳ እነርሱ የሚሰሩት ስውር ደባም ቢጋለጥ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንደሚያጡ ስለሚያውቁ የተለያዩ ድርሳኖችን ገድሎችን መልኮችንና ተአምሮችን ብቻ እንዲያነብ የሚያበረታቱ የሀይማኖት ካባ ያጠለቁ የበግ ለምድ የለበሱ የቀበሮ ባህታውያን ናቸው።

በመጨረሻው ዘመን እንደነዚህ ዓይነት ሐሰተኞችና አስመሳዮች በክርስትና ስም የሚነግዱና ራሳቸውን በሃይማኖት ጭምብል ውስጥ የሸሸጉ እንደሚነሱ ተጽፉአል። እነርሱንም መርምሮ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ንስሐ ካልገቡና ካልተመለሱ ማጋለጡ ኃጢአት ወይንም ወንጀል ሳይሆን በቃሉ መሠረት መጽሐፍትን መርምሩ ዘመኑን መርምሩ መንፈስን መርምሩ ራሳችሁን መርምሩ ተብሎ ስለ ተጻፈ መንፈሳዊነት እንጂ ሥጋዊነት አያሰኝም። *ማቴ.22:29፤ 1ዮሐ.4:1፤ ኤፌ.5:16፤ 1ቆሮ.11:31*

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች በሀይማኖት ሽፋን ለሰይጣን ዓላማና ለሥጋቸው አጀንዳ የሚኖሩ ወደ አዲሱና እውነተኛው ሚሊኒየም እንዲገቡ እግዚአብሔር አይፈቅድላቸውም። *ማቴ.25:11-12፤ ሉቃ.13:25-28*

## ክፍል አስራ አንድ

# የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር፣ የአርማው ምንነትና ትርጉም

### 1.1.1 ከመንግሥት የተሰጠ ትኩረት

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ክፍሎች ስለ ኢትዮጵያ ጥናታዊ ስልጣኔ ባህልና የዘመን አቆጣጠር በሰፊው ታትቷል።

ስለሆነም ከዚህ የዘመናት ቀመር በመነሳት ሀገሪቱ ስትጠቀምበት በኖረችው ልዩ የሆነ ካላንደር (0ውደ-ዕለት) 2ኛው ሚሌኒየም ወይም 2000 ዓ.ም የሚከበርበት ሁኔታ የወቅቱ ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ አብዛኛውን የዜና ሽፋን አግኝቶ ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለሚሌኒየሙ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት አስተባባሪ ኮሚቴዎች በሀገር አቀፍ በክልሎች በዞኖች በወረዳዎችና በቀበሌዎች እንዲሁም በየመሥሪያ ቤቱና በመንግሥታዊ፣ ህዝባዊና ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ውስጥ እንዲቋቋሙ አድርጓል። እነዚህ ኮሚቴዎች የተሰማሩበትን የማስተባበር ስራ እንዲያከናውኑ ቢሆንም የሕብረተሰቡ ፍላጎት ደግሞ ይህ ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ሳይቋረጥ ቢቀጥል ለሀገሪቱ እድገትና ለታሰበው ልማት ፈር ቀዳጅ እንደሚሆን ያምናል።

መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ የጀመረበት ምክንያት በዚሁ በሚሌኒየም በዓል ሰበብ የሀገሪቱ ልማትና ዕድገት ለማፋጠን እንደሆነ በመተለም ነው። የህዝቡ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ የሚከበሩበትን በስልጣኔና





በልማት ያደገችውን ኢትዮጵያን ተባብረን እንገንባ የሚል ሀሳብ ያለበት ነው።

ስለ ኢትዮጵያ ሚሌኒየም በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች በቴሌቭዥን በሬዲዮ ለበርካታ ጊዜያት የተነገረ ሲሆን በጋዜጣ በመጽሔት በመጽሐፍት እንዲሁም በአልባሳትና በጌጣጌጥ ዕቃዎች ላይ ተጽፎ ተሰራጭቷል።

ይህ እጅግ ልዩና የብዙዎችን ትኩረት የሳበ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም በሀገር ልማትና በእድገት አቅጣጫ በህዝቡ ኑሮና ህይወት ላይ አዎንታዊ ለውጥ ያመጣል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል።

በዚህ የሚሌኒየም በዓል በርካታ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትወልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ኢትዮጵያን የሚወዱ የውጭ ሀገር ዜጎች ተጋብዘዋል።

እነርሱም በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም በሚፈልጉት ሥራና የሙያ መስክ ኢንቨስት ቢያደርጉ ራሳቸውን ጠቅመው ለሌሎችም ዜጎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩ ታምኖበታል።

ስለሆነም ማዕከላዊ መንግሥት የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር ምክር ቤትና እንዲሁም የክልልና የዞን ከተማ ምክር ቤቶች ለእነዚህ ዜጎች የሚያስፈልገውን መሬት ለመስጠት ቅድመ ዝግጅት አድርገዋል። ይህም ልማትን ለማፋጠን ካላቸው ብርቱ ፍላጎትና ለሀገር ዕድገት መሆኑ ይታወቃል።

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ርዕሰ ከተማ፣ የበርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ቢሮዎች የአፍሪካ ሕብረት ጽ/ቤት ያሉበትና እንዲሁም የተለያዩ ሀገሮች ኢምባሲዎች መገኛ ነች። ስለዚህም በዓሉ የታለመበትን ግብ እንዲመታ ብርቱ ጥንቃቄና የህዝቡ የተለመደ ተሳትፎ ታክሎበት በዓላማው መሠረት ወደፊት መቀጠሉ አማራጭ የሌለው መሆን ይገባዋል። በተለይም

3ኛ/ የሴት ብልት (ማህጸን) ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች መገኛ ስለሆነች ይህ የሴት አካል ተመርጦአል የሚል ሦስት ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

ለአርማነት የተመረጠውና ከፍ ብሎ የሚታየው ስዕል ወይም ቅርጽ ግን ከተጠቀሱት ከሦስቱ ሀሳቦች ወደ ሦስተኛው ያደላል፡፡

ታዲያ ሀሳቡ ይህ ከሆነ 3ኛው ሀሳብ ነው ተብሎ ለብዙ ጊዜ ታስቦበት በዚህ በሚሌኒየም ዝግጅት በአርማነት የቀረበውና ሕዝብ እንደባንዲራ እያውለበለብ እንደባጅ በደረቱ ላይ እየለጠፈ እንደመለዩ (ኮፍያ) በራሱ ላይ እያደረገ በልብሱ ላይ ስዕሉን አሠርቶ እየለበሰ ያለው የሴት ማህጸን ከሚሌኒየም ጽ/ቤት በተሰጠው ምላሽ መሠረት ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች መገኛ ስለሆነች ነው ተብሎ የቀረበው ሌላ ተመሳሳይ ነገር ለምን አልቀረበም ወይም ደግሞ ይህ እውነት ከሆነና ሌላ ስውር ነገር ከሌለው የሴት ብልት ለምን ተመረጠ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡

በኢትዮጵያ ወደ 1ኛው ሺህ ዓመት መጨረሻ የነገሡት ነገሥታት በነበሩበት ዘመን ልዩ ልዩ የጥንት ሥልጣኔ ነጸብራቆች ተሠርተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የአክሱም የመቃብር ሐውልቶችና ሌሎች በየስፍራው የሚገኙ አብዛኞዎቹ ሐውልቶች የተሰሩት በወንድ ብልት ቅርፅ ሲሆን ትርጉሙም ሟቹ ንጉሥ ከፀሐይ አምላክ ከአይሬስ (ጣዖት) ጋር በመንፈስ ይገናኛል (ግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደርጋል) ልጆችም ለኢትዮጵያ ይወለዳሉ ተብሎ [illegible] እንደነበረ ይነገራል፡፡ የአይሬስ መቅደስ ፍርስራሽ በአክሱም ከተማ አጠገብ በጴንጠሊዮን ተራራ ሥር በ1905 ዓ.ም በአንድ ጀርመናዊ አሳሽ (አገር ጎብኚ) ስለመገኘቱ (the hand book of ancient and medieval history of Ethiopia up to 1855) በሚል መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል፡፡





ይህንን ሁኔታ ከሥር ስንመረምረው ሰይጣናዊ አሠራር ስለነበረና የእግዚአባሔርን ፈቃድና ሀሳብ ሳይሆን ነገሥታቱ የራሳቸውን ዓላማ ለማሳካት ሲሉ በህይወተ ሥጋ እያሉ የሠሩት አመጽና ክፋት ሳያንስ ሞተውም ኃጢአት እንዲሠሩ ተብሎ ሐውልት ተሠርቶላቸው ነበር፡፡ በተጨማሪም አንድ ንጉሥ ሲሞት የቅርብ አገልጋዮች (ባሮች) የሆኑት ፋከራና ቀረርቶ እያሰሙ ንጉሡ እንዲቀበር ወደተዘጋጀለት ጉድጓድ እየዘለሉ ይገቡና ነፍሳቸው ሳይወጣና ሳይሞቱ ከንጉሡ ጋር ይቀበሩ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ እርግማን የነበረውን የሀገሪቱን የሥልጣኔ ደብዛ አጥፍቶ ኢትዮጵያ በጨለማ የኋሊት ተጉዛ በድንቁርናና በድህነት አዘቅት ውስጥ እንድትወድቅ ምክንያት ሆኖአል፡፡

ዛሬስ ይህ የሚሌኒየም አርማ ምንን ለማሳየት ተፈልጎ የተመረጠ ነው? ወይስ ለማን ለማስተዋወቅና ከማንስ ጋር በመንፈስ ወይም በሥጋ ለመገናኘት ታስቦ ነው? አውቀውም ሆነ ሳያውቁት እግዚአብሔርን የሚያሳዝንና ህብረተሰብን የሚጎዳ ነገር መሥራት ለውድቀት እንጂ ለዕድገት አይሆንምና መጠንቀቅ ያሻል፡፡

## 11.4 የተስፋው ቃል ማስረጃ ለኢትዮጵያ

ስለ ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *በመዝ.68፡31 «ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች»* ተብሎ የተጻፈው ቃል የሚፈጸምበት ዘመን መቃረቡን የሚያሳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሚል ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከአርባ ጊዜ በላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ይህም እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ የገባውን ቃልኪዳንና ያለውን መልካም ሀሳብ የሚገልጽ ክፍል ነው፡፡ *መዝ.74፡14* ላይ ደግሞ *«የሌዋታንን (የዘንዶውን) ራስ ቀጠቀጥህ ለኢትዮጵያም ሰዎች ምግባቸውን ሰጠሃቸው»* ተብሎ ተጽፎአል፡፡ ዘንዶና ሌዋታን የተባለው ሰይጣን

የሚቀጠቀጠው በሰው ጡንቻ ሳይሆን በክርስቶስ ኃይል ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው የሰይጣንን ሥራ ጥንቆላን ውቃቢን ዛርን ቦሮንቲቻን ድግምትንና መተትን ወዘተ... ሲጠሉ፣ ሲተዉና በክርስቶስ ስም እነርሱን በመቃወም ሥራቸውን ሲያፈርሱ ብቻ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የሥልጣኔና የእድገት ጭላንጭልም የሚታየው ከእግዚአብሔር ምህረትና ቸርነት የተነሳ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የተከፈተው የምህረት በር እንዳይዘጋና እንቅፋትም እንዳይገጥመው ከፍተኛ ቅንነት ያለበት ጥንቃቄና ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያነሳሳ ክፋትና ርኩሰት ማድረግ ከተጀመረ በትላንትናው ትውልድ ላይ የደረሰ የጨለማውና የድንቁርና አደጋ ዛሬ አይደርስም ማለት አይቻልም፡፡

*‹‹የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?›› አሞ.9:7* ተብሎ የተፃፈው እግዚአብሔር ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ያለውን ፍቅር የሚገልፅ ነው፡፡

ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ እግዚአብሔርን እንደቃሉ ማወቅ መታዘዝ መፍራትና ማምለክ ይገባዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ሕዝቡ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ሁለት ሺህኛ ዓመት (2ኛ ሚሊኒየም) ለአንድ ዓመት እንደማንኛውም ተራ በዓል ማክበር ወይም ዘየአደባባዩ መጨፈር ብቻ ሳይሆን ትርጉሙ ገብቶት ተገቢውን መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

ሚሊኒየም ማለት የሺህ ዓመት የሰላም የፍቅርና የፀጥታ ዘመን ሆኖ ክርስቶስ ዓለምን የሚገዛበት ዘመን እንደሆነ *በራዕይ.20:1-4* ተብራርቷል፡፡ በዚያን ዘመን ሰይጣን ለሺህ ዓመት ይታሰራል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ዳግም ሲመለስ የእርሱ የሆኑት አብረው ይነግሣሉ፡፡ ሌሎች ሙታን ግን እስከ መጨረሻው ፍርድ ቀን ድረስ ከመቃብር አይነሡም፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያውን ትንሳኤ ወይም መነጠቅን ማግኘት





ትልቅ ዕድልና ለመጨረሻውም የዘላለም መንግሥት ወሳኝ ስለሆነ እያንዳንዱ ሰው በጥልቅ ሊያስብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

## 11.5 የህዝብ ቆጠራ ለዘላቂ ልማት

የኢትዮጵያ መንግሥት ያካሄደው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ለዘላቂ ልማትና እድገት አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ የህዝብን ብዛት እና የኑሮ ደረጃውን ለማወቅ እንደሚጠቅምና የወደፊት ልማት ዕቅድ ለመንደፍም እንደሚረዳ ይታመናል፡፡

በዓሉን ለማክበር ከላይ እንደተጠቀሰው የተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ግለሰቦች በከፍተኛ ደረጃ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ የእነዚህን እንቅስቃሴ አዎንታዊ ምላሽ ሊሆን የሚችለው የህዝቡ ዘላቂ ትብብርና ለሀገር እድገት ያለው ተነሳሽነት ተጠናክሮ ሲቀጥል ብቻ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብም የሥራ ባህሉንና አመለካከቱን መቀየር የግድ ነው፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ በየአቅጣጫው በከንቱ የሚፈስሱትንና የሀገሪቱን ለም አፈር ተሸክመው ወደ ጎረቤት አገሮች የሚሄዱትን ወንዞችና ጅረቶች በአግባብና በሥርዓት ለልማት መጠቀም እንዲቻል መንግሥት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በከርሰ ምድር ውስጥ ያሉትን ማዕድናትና ነዳጅንም ለማውጣትና በጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

በሀገሪቱ የመሬት አጠቃቀምም ረገድ ያለው አስተሳሰብ ተለውጦ አፈሩ በስራ ላይ ቢውልና ቢለማ ከህዝቡ ፍጆታ አልፎ ሌሎችን ሀገሮች ሊመግብ እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡ ይህ ሁሉ ለአንድ ሰሞን ብቻ በስሜታዊነትና በሞቅታ የሚደረግ

ሳይሆን ተደጋግሞ እንደተገለጸው ለዜጎች እድገትና ለዘላቂ ልማት ተግቶ መሥራትና ክትትል አስፈላጊ ይሆናል። ሕዝቡ መልካም አስተዳደር ካገኘ ውጤት ያለው ሥራ ይሠራል። የሀገሪቱም የድህነት ታሪክ ይለወጣል። እግዚአብሔር ምድሪቱንና ሕዝቡን ይባርካል።

## 11.6 እርቅ፣ ሰላም እና መቻቻል በሚሌኒየም

በኢትዮጵያ መንግሥት በሚሌኒየሙ ዋዜማ ከተደረጉት ትልቅና አመርቂ ተግባሮች አንዱ ለእስረኞች የተሰጠው ምህረት ነው። ይህ መቻቻልና ሰላምን የመፍጠር ባህል ለወደፊትም ሊበረታታ የሚገባውና የህዝቡንም ጥያቄ የመለሰ ነው። ይህም ብስለትንና ከቂምና ከበቀል ነጻ መሆንን የሚያስረዳ መልካም ምሳሌነት ስለሆነ ሌሎችም ይህንኑ በመመልከት እርቅና ሰላም እንዲፈጥሩ ያሻል።

ስለዚህ ተመሳሳይ መቻቻልና እርቅ በቤተሰብ በሕብረተሰብ በተለያዩ ጎሳዎች በብሔር ብሔረሰቦች በሀይማኖት ድርጅቶችና በግለሰቦችም መካከል መፈጠር አለበት።

ወደ ሚሌኒየሙ ለመግባት ቂምና በቀል እንግቦ መጓዝ የማያስፈልግ እንደሆነ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል።

አንዳንድ ግለሰቦች በቤተ ሃይማኖት ሆነ በቤተ መንግሥት የራሳቸውን የግል ፍላጎትና የስልጣን ጥማት ለማርካት ሲሉ ሕብረተሰቡን በተለያዩ ዘዴዎች አምሠው በስልጣን ኮርቻ ላይ የሚወጡ በየዘመናቱ አልጠፉም።

በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ እንደባህል ተለምዶና ሥር ሰዶ የቆየው የነገሥታትና የአልጋ ወራሾቻቸው የሥልጣን ሽኩቻ ነው። ‹‹ሁለት ዝሆኖች ሲጣሉ የሚደቀው ሳሩ ነው›› እንደሚባለው በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊው ኑሮ በመንፈሳዊ ህይወቱ የሚጎዳው ህበረተሰቡ እንጂ እነርሱ አይደሉም።





ነገሥታት በዙፋን ላይ ሲወጡ የመጀመሪያው አድርገው የሚወጥኑት ምናልባትም ሊጋፉን ወይም ሊቀናቀኑን ይችላሉ ብለው የሚገምቷቸውን የግል ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ወንድም እህቶቻቸውንና አባት እናታቸውን ሳይቀር መግደል ካልሆነም ገዳም ገብተው ራሳቸውን ከሸሸጉ ባሉበት ቦታ በግዞተኝነትና በቁም እስረኝነት እስከ እድሜ ልክ ድረስ ማቆየት ነዉ።

ይህ የመፈንቅለ ወንበር ባህል በቤተ ሃይማኖቱም ውስጥ ዘልቆ ገብቷል። የሃይማኖት አባቶች የተባሉና ሕብረተሰቡ በትልቅ ዓይን የሚያዩዋቸውና እንዲህ ዓይነት ተግባር የፈጽማሉ ብሎ የማይገምታቸው ሰዎች ከተጠሩበት ዓላማ ውጪ ክፉ ተግባር ሲፈጽሙ ማየት እየተለመደ መጥቷል።

ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቀው ያውቃሉ በመንፈስ ቅዱስም ይመራሉ በሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህ ሁኔታ እየተዘወተረ ችግር እየሆነ ነው። አንዳንድ ጊዜ ምዕመኑም የእነዚህን መንፈሳዊ መሪዎች ዓላማና እውነተኛ የደህንነት ማግኘት ጉዳይ እንኳን እየተጠራጠረ ይገኛል።

ይህ ሁኔታ በተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ ያለ ችግር ቢሆንም መሪዎች በሃይማኖቱ መመሪያና ደንብ መሠረት ካልመሩ ህዝቡን ከእነርሱ የባሰ ሸፍጠኛ ሊሆን እንደሚችል ሊረዱ ይገባል።

የአሁኑ ጊዜ የመጨረሻ ዘመን መጨረሻና እውነተኛው ሚሌኒየም (የሺህ ዓመት መንግሥት) እና የመጨረሻው ፍርድ ሰዓት መቃረቡን የሚያመለክቱ ፍንጮች በጉልህ እየታዩ ነው። በዚህ ጊዜ እራስን አዘጋጅቶ ሌሉችም የጽድቅ ልብሳቸውን ለብሰው የሚመጣውን ሙሽራና የተባረከ ተስፋችን ተብሎ የተጠቀሰውን ኢየሱስ ክርስቶስን በአየር እንዲቀበሉ ማዘጋጀት

እንጂ ለዓለማዊ ሥልጣንና ለንዋይ መገዛት ዓላማን መሳት ይሆናል።

ነገር ግን ይህንን እያወቁ በሽፍጥና በቃላት በማታለል በሥልጣን ላይ ለወጡትም ምናልባት ዓይናቸውን ጨፍነው በሃይማኖት ጭምብል ውስጥ ሊገቡ ቢሞክሩም እርቃናቸውን የሚቀሩበት ቀን በደጅ መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም። ስለዚህ በመንግሥት ስልጣንም ሆነ በቤተ ሃይማኖት መሪነት ወንበር ላይ ያሉ ሁሉ ከእግዚአብሔርና ከህዝብ የተሰጣቸውን አደራና ሃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንጂ በሥልጣን ሽኩቻና በአሉባልታ ጊዜያችን ማጥፋት አይገባቸውም፤

## 11.7 የኢትዮጵያ ህዳሴና የሚሌኒየሙ በዓል

ጳጉሜ 6/1999 ዓ.ም ለመስከረም 2000 ዓ.ም አጥቢያ አሮጌውን ዘመን ለመሸኘትና አዲሱን ዘመን በደስታ ለመቀበል የተከበረው በዓል እጅግ ደማቅ ነበር። በዓሉ በአዲስ አበባ ከተማ በስቴዲየም፣ በጃንሜዳና በቦሌ የሚሌኒየም አዳራሽ ሲከበር በየክልልና በዞን እንዲሁም በወረዳና በየቀበሌው በገጠርና በከተማዎች በከፍተኛ ስሜት ተከብሮአል። በእለቱ የየክልሉ ፕሬዚዳንቶች የመልካም ምኞትና የወደፊት ራዕይ መግለጫ የሰጡ ሲሆን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ) ፕሬዚዳንት ጠቅላይ ሚኒስትርና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የሚሌኒየም በዓሉ የበላይ አስተባባሪ በየተራ ንግግር አድርገዋል። በንግግራቸውም ያተኮሩት በአገሪቱ ልማት በህዝቡ እድገትና ድህነትን ታሪክ አድርጎ ለማስቀረት ጠንክሮ መሥራት ተገቢ እንደሆነ ሲገልጹ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ 10% ዕድገት መመዝገቡን አብራርተዋል።





በተጨማሪም ያለፈውን ሚሌኒየም ያከበረው ትውልድ የዛሬ አንድ ሺህ ዓመት እንዴት እንዳከበረ የተጻፈ መረጃ ባይኖርም በጊዜው በነበረው መንፈሳዊና ቁሳዊ ይዘት በደማቅ ሁኔታ አክብረው እንደነበረ መገመት እንችላለን።

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ያላት ሀገር ስትሆን ታሪኳም የነፃነት ታሪክ ነው። በተለይም በየዘመናቱ አፍሪካን ለመቀራመት ከተነሱት ከባዕድ ኃይሎች የተሰነዘረባትን ወረራ በመመከት ለዛሬው ነፃነታችን አብቅተውናል። ይሁን እንጂ አገሪቱ በእድገት ደረጃ የኋሊዮሽ ከመሄዱዋ በስተቀር ለእድገት ሳትታደል ቆይታ በጨለማ ዘመን ውስጥ አልፋ እዚህ መድረሷን ገልጸዋል። አሁንም ቢሆን ላለፈው ተወቃሾችም ሆነ ለሚሠራው ትልቅ የልማት ሥራ ተመስጋኞች ሌላ ሰው ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ ያለን ትውልድ ስለሆንን ክንዳችንን አስተባብረን ለእድገትና ለድህነት ቅነሳ የሚደረገውን ርብርብ እያንዳንዱ ዜጋ የራሱን አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚጠበቅበት ጠቅሰዋል።

በልማት በዴሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ግንባታ ረገድ የላቀ ተሳትፎ በማድረግ ለተያዘው አገራዊ ራዕይ ክንዋኔ ተባብሮ መሥራት እጅግ ተገቢ እንደሆነም ተገልጾአል።

ከዚሁ ጋር በሀገሪቱ ብዙ ብሔሮች ብሔረሰቦችና የተለያዩ ሃይማኖት እምነቶች ተከባብረው የሚኖሩባት እንደሆነ በመግለጽ ለወደፊቱ የብሔር የቋንቋ የሃይማኖትም ሆነ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ቢኖርም የመቻቻል ባህላችንን አዳብረን መቀጠል ተገቢ ነው በማለት ለአንድ ዓመት በሚቆየው በዚህ ሚሌኒየም ዲያስፖራውም ሆነ የሀገር ቤቱ ነዋሪ በልማት ተሳትፎው የየበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ መንገድ ተከፍቷል።

በተመሳሳይ ወደ ሦስተኛው ሚሌኒየም ስንገባ መቻቻልና መግባባትን ባህላችን አድርገን ለኢትዮጵያ ህዳሴ አገራዊ ራዕይ መገስገስ አለብን ብለዋል።

ስለዚህ መሪዎች እንደተናገሩ ጥቂት የክልል አስተዳዳሪዎችም እንዳደረጉት በፖለቲካም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች ማረሚያ ቤት የሚገኙት ታራሚዎች ሁኔታቸው እየተጠና መታረማቸውን በማረጋገጥ የሚለቀቁበትና መቻቻሉ ተግባራዊ የሚሆንበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ በቤተ ሃይማኖት በብሔርችና በተለያዩ ጎሳዎች መካከል ያለውም የእርስ በርስ ቁርሾችና ቂም በቀል የሚወገድበት በቤተሰብ ደረጃም በባልና ሚስት በልጆችና በወላጆች መካከል ያለው ግጭትና መለያየት የሚወገድበትን አጥብቆ መፈለግ ያሻል፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው በሙግት ሳይሆን "በመሸነፍ ማሸነፍ" በሚባለው የመቻቻል ስልት ነው፡፡ *‹‹ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ›› ሮሜ.12:21*

እንግዲህ ይህ የተያዘው ሦስተኛው ሚሌኒየም ማለት 2000 ዓ.ም ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በሙሉ ቢስተካከሉና አንድ ልብ ኖሮ ለአንድ ዓላማ መነሳት ቢቻል ምድሪቱ በሆድዋ ውስጥ ያረገዘቻቸውን ማዕድናትና ነዳጅ እንድታፈልቅና በላይዋ የተሸከመችው ሀብት በሥራ ላይ ቢውል ድህነት ታሪክ ብቻ ሆኖ እንዲቀር እግዚአብሔር ያደርጋል፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ መካከለኛ ገቢ ካለቸው አገሮች ጎራ ለመሰለፍ እንደተባለው ሠላሳ ዓመት ሳይጠበቅ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ትልቅ ለውጥ ሊመጣ እንደሚችል ይታመናል፡፡ ለውጥና ዕድገት የሚመጣው ግን በዳንስ በዳንኪራና በጭፈራ ሳይሆን ጠንክሮ በመሥራትና እግዚአብሔርን በመፍራት ነው፡፡ *‹‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው›› ምሳ.1:7*





## ክፍል አስራ ሁለት

# የኢትዮጵያ ሚሌኒየም የአፍሪካ ሚሌኒየም መባሉ

### 12.1 የአፍሪካ ህብረት ውሳኔ

የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ የኢትዮጵያን ሚሌኒየምን በተመለከተ ተነጋግሮ ይህ የኢትዮጵያ ሚሌኒየም የአፍሪካም ሚሌኒየም ሆኖ እንዲከበር ወስኗል፡፡

ይህም ውሳኔ በራሱ ለኢትዮጵያ ሚሌኒየም የተሰጠውን ትልቅ ስፍራ የሚያስረዳ ከመሆኑም በላይ የአፍሪካ ሀገሮች ለሚሌኒየሙ ያላቸውን ትኩረት፣ አንድነትና ህብረት የሚያሳይ ክስተት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ በርካታ የአፍሪካ ሀገሮች ተሳትፏቸውን በተለያየ ሁኔታ ገልጸዋል በመግለጽም ላይ ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ የአፍሪካ ሀገሮች በኢትዮጵያ ባሉት ኢንባሲዎቻቸውና በሀገሮቻቸው ቁልፍ መሪዎች አማካኝነት አፍሪካውያኑ በሚሌኒየሙ ስም የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እያደረጉ ከመሆናቸውም በላይ ለወደፊቱም ለዘላቂ ልማትና እድገት የበለጠ ጥረትና ተሳትፎ እንደሚያደርጉ የተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች እያስተላለፉ ነው፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለኢትዮጲያ ሚሌኒየም እውቅና ከመስጠቱም በላይ የቅርብ ትኩረት እያዳረገ ሁኔታውን በአጽንዖት በመከታተል ላይ ነው፡፡

የዓለምን ትኩረት በእጅጉ የሳበው ይህ ሚሌኒየም ስለኢትዮጵያ ያላቸውን የብዙዎችን የተዛባ አመለካከት ይለውጣል ተብሎ ይታመናል። ኢትዮጵያ የምትታወቀው በጦርነት፣ በቸነፈር፣ በረሀብ በድህነት ብቻ እንደሆነ የሚገምቱ ሰዎች ሀሳባቸውን እንዲቀይሩ ትኩረት ተሰጥቶ እውነቱን ለማሳየት ተገቢው ሥራ እየተሠራ ይገኛል። ይህ ሁኔታ ሳይቋረጥ ቢቀጥልና በውጭ ያሉ ኢትዮጵያንም በሀገራቸው መጥተው በተለያዩ የልማት ዘርፎች እንዲሳተፉ ቢደረግ የምንመኘው ዕድገት ውጤቱ በቶሎ ይታያል።

## 12.2 የትላንቱ የድህነት ታሪክ

በኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር የአየር ጠባይ ሆነ የአፈር ለምነት ጠፍቶና የማይመች ሆኖ ሳይሆን ለረዥም ዘመናት ለህዝቡ እድገት ልማትና ለውጥ ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራና የሚያሠራ መሪ ጠፍቶ ህዝቡ በድህነት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆ ኖሯል።

ስለዚህ አሁን የኢትዮጵያ ድህነትና ችግር የትላንት ታሪክ ብቻ ሆኖ የሚቀርበትን ሁኔታ ለመፍጠር እያንዳንዱ ዜጋ ሙሉ አቅሙን በመጠቀም መንቀሳቀስ ይኖርበታል። ይህ ከሆነና የሀገር መሪዎችና በተለያየ ደረጃ ያሉ ባለሥልጣናት የትኩረት አቅጣጫቸውን በዚህ የሀገር ልማትና እድገት ላይ አድርገውና ከአድልዖ፣ ከሙስናና ከቂም በቀል ከተለዩ እነርሱም ሆኑ ህዝቡ የሚመኘው ልማት፣ በረከትና እድገት ተግባራዊ ይሆናል። ይህ ካልሆነና ቃል ብቻ ሆኖ ተግባር ከሌለው የህልም እንጀራ ሆኖ እንደሚቀር መታወቅ አለበት።

*«እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ እንቢ ብትሉ ግን ብታመጹም ሰይፍ ይበላችኋል የእግዚብሔር አፍ ይህንን ተናግሮአልና» ኢሳ.1፡19-20*





አፍሪካውያንንና ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ለዚህ ለተቀደሰ የልማትና የሰላም ዓላማ ከኢትዮጵያ ጎን ከተሰለፉና እያንዳንዱም ሰው የድርሻውን ከተወጣና እግዚአብሔርም ከተጨመረበት በጎ ዓላማው ግቡን የማይመታበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

## የሚሌኒየሙ በዓል ወቅት ስጋት

ይህ ትልቅ ቦታና ትኩረት የተሰጠው የሚሌኒየም በዓል ለአንድ ዓመት የሚከበር እንደመሆኑ መጠን ሀገሪቱን በኢንቬስትመንት ለማልማት የመጡ መኖራቸውን ያህል የሰይጣንን ስውር ዓላማ ለማስፈጸምና የራሳቸውንም ርካሽ ስሜት ለማርካት የመጡ ይሆናሉ ብሎ መገመት ተገቢ ነው። ሌሎች ደግሞ በሀገሪቱ ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያነሳሳና መቅሰፍት የሚያስከትል እንደአደንዥ እፅ እና ሐሺሽና እንዲሁም ለግብረሰዶም የመጡ ካሉ ወጣቶችን እንዳይለክፉ አስፈላጊውን ጥበቃ ማድረግ ተገቢ ነው። ይህ ካልሆነ ግን ለመልካም ዓላማ የታሰበው የሚሌኒየሙ በዓል ሌላ ያልተፈለገ መዘዝ እንደዳያመጣ ያሰጋል።

ስለዚህ መንግሥትና ሕብረተሰቡ ዜጎችን ከክፉ ባህሪይ ለመከላከልና ሌላ እርግማን በምድሪቱ ላይ እንዳይመጣ ለማድረግ በተቀናጀ መልኩ ክፉውን መከላከልና ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል።

## ክፍል አስራ ሦስት

# የኢትዮጵያ የእንግዳ አቀባበል በሚሌኒየም

### ሊደረግ የሚገባው የቅርብ ክትትል

የኢትዮጵያ ሚሌኒየም ከፍ ብሎ እንደተገለጸው የተለያዩ ባህሪያት ያሉአቸው የብዙ ሀገር ዜጎች የሚሳተፉበት እንደመሆኑ መጠን እንደተጠቀሰው ስጋት መፍጠሩም የማይቀር ጉዳይ ነው:: ይኸውም ወደ ሀገሪቱ የሚገቡ እንግዶች በሙሉ በሥነ ምግባር የታነፁ ፍፁም ናቸው ብሎ ማመን አጉል የዋህነት ካልሆነ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም::

በሀገሪቱ ላይ ለብዙ ዘመናት የተንሰራፋው የመናፍስት አሠራር ለድህነትና ለችግር ዳርጓት እያለና ህዝቡም ገና ካለፈው ሁኔታ ወጥቶ የችግሩ ሳንካ ሳይነቀል ተጨማሪ እርግማን ጎትቶ እንዳያመጣ ያሰጋል::

የኢትዮጵያውያን የእንግዳ አቀባበል ባህል በራሱ መልካም ገፅታና አስተዋፅዖ ያለው መሆኑ ባይካድም ከታሪክ የምንረዳው መጥፎ ጎንም እንዳለው ነውና ድጋሚ ጥፋት እንዳይሆን ብርቱ ጥንቃቄና የቅርብ ክትትል ተገቢ ይሆናል:: ይህ ካልሆነና በቸልታ ከታለፈ ዛሬ የሚተከለው ትንሽ የሚመስል መራራ ፍሬ በቅሎ ‹‹በሁለት ጣትህ ልትነቅለው የምትችለውን ዐረም በሁለት እጅህ መንቀል እስኪያቅትህ ድረስ አትጠብቅ›› እንደሚባለው ነውና ማንኛውም ሁኔታ ከእይታ ወጪ መሆን የለበትም::

ይህ የሚሌኒየም ዝግጅትና ዜና መነገር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የብዙ ሰዎች ስጋትና ጸሎት እግዚአብሔር መልካም





የሰላም ጊዜ እንዲያደርግና ወደ ሀገሪቱ የሚመጡ እንግዶች በሰላም እንዲመለሱ ነው:: በተጨማሪም በመንግሥትም ሆነ በህዝብ የሚታሰበው የሀገሪቱ ዘላቂ ልማትና ሰላም ዜጎች እግዚአብሔርን በማወቅና በማምለክ ታዝዘው በነፍስም በስጋም እንዲባረኩ ከልብ እየተፀለየ ነው:: የሚሌኒየም በዓሉ ለአንድ ዓመት የሚቆይ ስለሆነ ትክክለኛዎቹ የሚሌኒየም እንግዶች ግን ሕብረተሰቡ በሙሉ ኢትዮጵያዊ ባህሉን በጠበቀ ሁኔታ ማስተናገድ ይገባል:: እነዚህ ሰዎች የኢትዮጵያውያንን ደስታ ለመካፈል እስከመጡ ድረስ ምንም ዓይነት እንግልት ሊያደርስባቸው አይገባም::

ነገር ግን እሳት ከሰማይ ወርዳ በማቃጠል ይመልሳቸዋል። ያሳታቸው ዲያቢሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት በዲን በሚቃጠል እሳት ባህር ውስጥ ተጣሉ ሌሊትና ቀን ለዘላለም ይሰቃያሉ። *ራዕይ.20፡4-10*





## ክፍል አስራ አምስት

# ሦስቱ የሚሌኒየም አመለካከቶች

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል በተመለከተ ስለ ሺህ ዓመት መንግሥት (millennium) ሦስት አመለካከቶች አሉ።

እነዚህም አመለካከቶች፡-

1. አልቦ ሺህ ዓመት ውስጥ ነን (AMillennialism)
2. ድህረ ሺህ ዓመት (Postmillennialism)
3. ቅድመ ሺህ ዓመት (Premillennialism)

በመባል ይታወቃሉ።

## 15.1 አልቦ ሺህ ዓመት መንግሥት ውስጥ ነን የሚሉ (AMillennialism)

ወደ ሺህ ዓመት መንግሥት ገብተናል የሚል (AMillennialism) አመለካከትና እምነት *ከራዕይ 20፡1-10* የተገለፀውን መሠረት በማድረግ ሀሳብ ሲያቀርቡ ይህ አሁን ያለንበትን የቤተ ክርስቲያን ዘመን የሺህ ዓመት መንግሥት ዘመን ነው ይላሉ። በዚሁ ጊዜ በምድር ላይ የሰይጣን ተፅእኖ በአብዛኛው የቀነሰ ስለሆነ በዓለም ሁሉ ወንጌል ሊሰበክ ይችላል ከክርስቶስ ጋር ሺውን ዓመት የሚነግሡ ቀደም ሲል በጌታ የሞቱና ከዚህ በፊት በሰማይ ከክርስቶስ ጋር በመንግሥቱ ያሉ

የዚህ እምነት አመለካከት መሠረቱ የመጽሐፍ ቅዱስ *‹‹...ጌታ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ሕያዋን ሆነን ምንገኝ የሞቱትን አንቀድምም። በትዕዛዝ ድምፅ በመላዕክት አለቃ ድምፅ የእግዚአብሔር መለከት ይሰማል ጌታ እራሱም ከሰማይ ይወርዳል በክርስቶስ አምነው የሞቱትም አስቀድመው ይነሳሉ። ከዚህ በኋላ እኛ በህይወት የምንገኘው ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ ለዘላለምም ከጌታ ጋር እንሆናለን›› 1ኛተሰ.4፡15-17*

ይህም የሚገልጸው ሳይጠበቅ በድንገትና በስውር ክርስቶስ አማኞች በደመና ሊጠራና ሊወስዳቸው ሲመጣ ቀደም ሲል በክርስቶስ ያንቀላፉት (የሞቱት) በቅድሚያ ይነሳሉ ከዚያም በሕያወት ያሉት ጌታን ለመቀበል ከእነርሱ ጋር ይነጠቃሉ ከዚህም ጌታ ወደ ሰማይ ይዞአቸው ይሄዳል።

## 16.2 እስራኤል በታላቁ መከራ ወቅት

አማኞች ከተነጠቁት በኋላ ታላቁ መከራ በምድር ላይ ለሰባት ዓመታት ይከሰታል። በእነዚህን ሰባት የመከራ ዘመናት ቀደም ሲል ስለ መጨረሻው ዘመን የተገለጹ ምልክቶች በአብዛኛው ይፈጸማሉ። እስራኤላውያንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሲሃቸው እንዲቀበሉ ይሰበክላቸዋል። በታላቁ መከራ መካከል ታላቅ የወንጌል ስርጭት ውጤታማ ይሆናል። በተለይም አዲስ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች የወንጌልን ስርጭት በኃይል ያካሄዳሉ።

ከሰባቱ የመከራ ዓመታት በኋላ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ጋር ወደ ምድር ይመለሳል፤ ለሺህ ዓመትም በምድር ላይ ይነግሣል። በሺው ዓመት መጨረሻ ሰይጣን ከታሰረበት ይፈታል፤ አመፀኞችንና ተቃዋሚዎችን ለመጨረሻው ጦርነት ያነሳሳል ነገር ግን በታላቅ አመታት ይሸነፋሉ። ቀጥሎም ያላመኑት ለፍርድ ይነሳሉ፤ በነጩ ዙፋን ፊትም ይቀርቡና





ይፈረድባቸዋል። አማኞች ደግሞ ወደ ዘላለም ሕይወት ይገባሉ ይህም የዘላለም መንግሥት ጅማሬ ይሆናል።

ከታላቁ መከራ ሰባት ዓመታት በኋላ የሚሆን የሺህ ዓመት መንግሥት የሚፈጸመው ከመከራው በፊት ቤተ ክርስቲያን በአየር ተነጥቃ ከምድር ላይ ከተወሰደች በኋላ ሰፊ ቁጥር ያለው የእስራኤል ህዝብ ከመከራው የተነሳ ትንቢት የተነገረለትን ሱባዔ የተቆጠረለትን መሲህ ሲፈልግ የሁኔታውን ትኩረት ልዩ ያደርገዋል።

ሌላው የዚህ አመለካከት የእምነት ባህሪይ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ትንቢቶች በትክክል እየተፈፀሙ መሆናቸውን ሲገልፅ በተለይም ስለ እስራኤል በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰው ሁሉ በተግባር የሚተረጎምበት ሁኔታ ይታያል። ይህንን በተመለከተ ሌሎች ምሁራን ስለ እስራኤል በመፅሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው የትንቢትዊ ቃል የሚፈፀመው እስራኤል ከቤተ ክርስቲያን በሚገኝ መንፈሳዊ በረከት ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ የሚሰጠው እንደሆነ ይገልጻሉ።

ዋናው የዚህ እምነት የትኩረት አቅጣጫ ግን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ በድንገት በማንኛውም ሰዓት ሊሆን ስለሚችል ለዚሁ በዝግጅት እንድንጠብቅ የሚያስገነዝብ መሆኑ ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ በቃሉ ላይ የተነገረውና በምድር ላይ የሚደረገው የመጨረሻው ዘመን ትንቢት እየተፈጸመ ስለሆነና በመከራው ዘመን ስለሚጠናቀቅ ነው።

## ክፍል አስራ ሰባት

# ስለ ሺህ ዓመት የተሰጡ ትርጉሞች

### 17.1 በአልቦ ሺህ ዓመት መንግሥት ውስጥ ነን የሚሉ ሰዎች (AMillennialism) የሚሰጡት ትርጉም

ስለ ሺህ ዓመት መንግሥትና ስለ መጨረሻው ዘመን ከላይ እንደተጠቀሰው የተለያዩ ሰዎች የሚሰጡት ትርጉም እንደግለሰቦቹ ግንዛቤና መረዳት የተለያየ በመሆኑ መጠነኛ የሀሳብ ልዩነቶች መኖራቸው ባይካድም አጠቃላይ ወደ ድምዳሜው ግን ተመሳሳይነት አለው፡፡ ስለሆነም ስለ ሺህ ዓመት መንግሥትም ሆነ ስለ መከራው ዘመን በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በእግዚአብሔር ጸጋ በመመራት መተርጎሙ ትክክለኛውን አቅጣጫ ያስይዛል እንጂ በፅንፈኝነት ወይም በአክራሪነት መጓዙ ለባሰ ስህተት ይዳርጋልና መጠንቀቅ ተገቢ ነው፡፡

### 17.2 ስለ አመለካከት ልዩነት

ስለ ሺህ ዓመት መንግሥት አሁን ባለንበት ዘመን እየተፈፀመ ነው ከሚሉ (AMillennialists) ምሁራን የትኩርት አቅጣጫ ልዩነት ስንመለከት ከዚህ በላይ ባለው ክፍል እንደተጠቀሰው ሁሉ የሚከተለውን የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል እናያለን፡፡ *‹‹ከዚህ በኋላ የጥልቁ ጉድጓድ መክፈቻና ትልቅ ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልዓክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ ዘንዶውንም ይዞ ሺህ ዓመት አሰረው፡፡*





*ይህም ዘንዶ ዲያቢሎስ ወይም ሰይጣን የሚባለው የቀደመው እባብ ነው፤ሺው ዓመትም እስኪፈፀም ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ ሕዝቦችን እንዳያስት መላዕኩ ዘንዶውን ወደ ጥልቁ ጉድጓድ ጣለው ዘግቶም በማኃተም አሸገው፡፡ ከዚህም በኋላ ለጥቂት ጊዜ መፈታት ይገባዋል፡፡*

*ከዚህ በኋላ ዙፋኖችን አየሁ በዙፋኖችም ላይ የመፍረድ ሥልጣን የተሰጣቸው ተቀምጠው አየሁ፡፡ ስለ ኢየሱስ ምስክርነትና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሳቸቸው የተቆረጡባቸውን ነፍሶች አየሁ እነርሱ ለአውሬውና ለምስሉ ያልሰገዱ ምልክቱንም በግንባራቸው ሆነ በእራሶቻቸው ላይ ያላደረጉ ናቸው፡፡ እነርሱ ከሞት ተነስተው ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ነገሡ፡፡ የቀሩት ሙታን ግን ሺው ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ከሞት አልተነሱም ይህም የመጀመሪያ ትንሳኤ ነው፡፡ የመጀመሪያው ትንሳኤ ተካፋይ የሆኑ የተመሰገኑ እና ቅዱሳን ናቸው፡፡ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ስልጣን የለውም፡፡ እነርሱም የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከክርስቶስም ጋር ሺውን ዓመት ይነግሣሉ›› ራዕይ.20:1-6* ይላል፡፡

### 17.3 የሰይጣን ጉልበት መስበርና መታሰሩ

በእነዚህ ምሁራን ግንዛቤ *በራዕይ.20:1-2* ባለው ክፍል ስለ ሰይጣን መታሰር የተገለጸው ክፍል በክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ወቅት የተፈጸመ ነው የሚል ሲሆን ራሱ*በማቴ.12:29* ሲናገር *‹‹...ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ንብረቱን መዝረፍ እንዴት ይቻላል? ኃይለኛውን ካሰረ በኋላ ግን ንብረቱን ሊዘርፍ ይችላል››* የሚለውን ሲተረጎሙና ከፍ ብሎም *በቁጥር 28* የተጠቀሰውን *‹‹እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ ከእንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች ማለት ነው››* የሚለው የሰይጣንን የመግዛት ጉልበት መስበሩን መታሰሩን እንዲሁም *በሉቃ.10:18-19* ደግሞ *‹‹...ሰይጣን እንደመብረቅ ተወርውሮ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁት››* የሚለውን በመጥቀስ ይህ የሰይጣን መታሰር ወደ ፊት የሚሆን ሳይሆን የተፈጸመ ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡ በተጨማሪም *ራዕይ.20:1-3* ካለው ክፍል *‹‹...ከእንግዲህ ወዲህ ህዝቦችን እንዳያስት...››* የሚለውን በመውሰድ ይህ በቀጥታ

አይሁድን ብቻ ሳይሆን ከጴንጤቆስጤ (ከበዐለ-ጳረቅሊጦስ) በኋላ ለዓለም ህዝቦች በሙሉ ወንጌል እንዲሰበክ ክርስቶስ መምጣቱን ያበስራል ይላሉ። በእርግጥ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ሁሉ ላይ የሚታየው የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ የሚያመለክተው በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎችን በጨለማ ዘግቶ ያቆያቸው የሰይጣን ኃይል በክርስቶስ መሰበሩንና አዲስ ኪዳን ለውጥ መምጣቱን ያሳየናል። በተጨማሪም በእነዚህ ምሁራን አመለካከት *በራዕይ.20:4* ያለውና *‹‹...ስለ ኢየሱስ ምስክርነትና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሶች አየሁ እነርሱም ከሞት ተነስተው ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ነገሡ››* የሚለው በሰማይ እንጂ በምድር ላይ በሥጋ የሚሆን አይደለም ማለታቸው ሲሆን ሌሎቹ የዚህ አመለካከት አራማጆች ይህንን ሀሳብ ሊተረጉሙ በሰማያዊ ስፍራ ከክርስቶስ ጋር መገኘትና ከእርሱ ጋር መንገሥን የሚገልጽ መሆኑን ለማሳየት ይሞክራሉ፤ በዚህ አመለካከት መሠረት ‹‹የመጀመሪያ ትንሳኤ›› የሚለው ወደ መንግሥት ሰማይ መሄድንና ከጌታ ጋር የመሆንን ሁኔታ እንጂ በሥጋዊ አካል መነሳትንና መንቀሳቀስ አይገልጽም ይላሉ *ቁጥር 5 ‹‹የቀሩት ሙታን ግን ሺው ዓመት እስኪፈጸም ድረስ ከሞት አልተነሱም።››*

ይህ ሀሳብ በግልፅ እንደሚያሳየው እነዚህ ሙታን በሺው ዓመት ለፍርድ በእግዚአብሔር ፊት አለመቅረባቸውን ይገልጻል። *በቁጥር 4-5* ባለው ክፍል ከሞት ተነስተው ህያዋን ሆኑ የሚለው ከእግዚአብሔር ጋር የሆኑትን ሲሆን ከሞት ያልተነሱት ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ፊት ያልቀረቡትን ለመግለፅ የተግፈ አባባል ነው ይላሉ። ከዚሁ ጋር የዚህ እምነት ተከታዮች የመጀመሪያው ትንሳኤ የሚለው የክርስቶስ ትንሳኤ ሲሆን ሁለተኛው የምዕመናን ከእርሱ ጋር በመተባበርና አንድነትን የመፍጠር ሁኔታ መግለጫ ነው ይላሉ። (systematic theology, 1115)





ሌላው የሚያቀርቡት ሀሳብ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው አንድ ትንሳኤ ብቻ ነው። ይኸውም ከአማኞችም ሆኑ ያላመኑ የሚነሱበት ወቅት አንድ ጊዜ እንጂ ሁለት ጊዜ አይደለም (አማኞች ከሚሊኒየሙ በፊት ያላመኑ ለፍርድ ከሚሊኒየሙ መጨረሻ)። ምክንያቱም ቅድመ ሺህ ዓመት መንግሥትን በሚያምኑት እምነትና አመለካከት በሺህ ዓመት የሚለያዩት ሁለት የትንሳኤ ጊዜያት የተጠቀሱ ስለሆነ ነው።

## 17.4 የተለየ የሙታን ትንሳኤ አመለካከት

አንድ ትንሳኤ ብቻ የሚሉ የሚጠቀሙባቸው ሶስት ጥቅሶች *‹‹...በመቃብር ውስጥ ያሉት ሁሉ የእርሱን ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካም የሠሩ ከሞት ተነስተው በህይወት ይኖራሉ፤ክፉ የሰሩ ግን ከሞት ተነስተው ይፈረድባቸዋል...›› ዮሐ.5:28-29*

በዚህ ክፍል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኞችና ያላመኑት ከመቃብር የሚነሱበትን ሰዓት ሲገልፅ በተመሳሳይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ በፊሊክስ ፊት ለተቃዋሚዎቹ አይሁዶች ሊገነዘቡት የሚገባ *‹‹...እነርሱም ተስፋ እንደሚያደርጉት እኔም ፃድቃንና ኃጢአን ከሞት እንደሚነሱ በእግዚአብሔር ተስፋ አደርጋለሁ›› ሐዋ.24:15* በዚህ ክፍል ሐዋሪያው አማኞችና ያላመኑ በትንሳኤ እንደሚነሱ ይናገራል። በመጨረሻም *በዳን.12:2-3* ላይ *‹‹አስቀድመው ከሞቱት ሰዎች ብዙዎቹ ተነስተው እንደገና በሕይወት ይኖራሉ። ከእነርሱም አንዳንዶቹ የዘላለም ሕይወት አግኝተው ሲደሰቱ አንዳንዶች ለዘላለም በሀፍረትና በጉስቁልና ይሰቃያሉ››* በዚያን ጊዜ ጠቢባን እንደ ሰማይ ብርሃን ያንጸባርቃሉ፤ ብዙ ሰዎችን በማስተማር ከክፉ መንገድ ወደ ደግ ሥራ የመለሱ ሁሉ ለዘላለም እንደ ሰማይ ከዋክብት ያበራሉ። በማጠቃለያው ሺህ ዓመት መንግሥት አሁን ጀምሯል የሚሉ (AMillennialism) እንደ ሚያምኑት ስለመጨረሻው ሰዓት የተፃፉ ትንቢቶች የዘላለም መንግሥት ከመጀመሩ በፊት

የጭንቀቱ ሰዓት በአንድ ጊዜ ይሁን በተለያዩ ጊዜያት እንደሆነ አያስረዳም። ይኹን እንጂ ሁለቱንም ዓይነት ሰዎች መነሳታቸውን ይገልፃል። በተመሳሳይ *ሐዋ.24፡15* ሐዋሪያው ጳውሎስ *‹‹…ጻድቃንም አመጸኞችም ከሙታን ይነሱ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝ››* ሲል ይህንኑ ያረጋግጣል እንጂ ትንሳኤ አንድ ጊዜ መሆኑን አያሳይም። *ራዕይ.20፡5-6* የተቀመጠው ግን ሁለት ትንሳኤ መኖሩን በግልጽ ስለሚያሳይ እርግጠኛነቱን በመረዳት እያንዳንዱ ሰው ወደፊት ሊሆን ያለውን ክስተት ማወቅና ከወዲሁ መጠንቀቅ ተገቢ ይሆናል።

## 18.2 ኑሮ በሺህ ዓመት መንግሥት ውስጥ

በሺው ዓመት መንግሥት (Millennium) በትንሳኤ የቀየረ አካል ያላቸው አማኞችና ኃጢአተኞች በምድር ላይ በአንድነት የመኖራቸው ሁኔታ ሲታሰብ ለማመን አስቸጋሪ ይመስላል። ነገር ግን ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ያደርገዋል ብለን እናምናለን። ክርስቶስ እራሱ ለአርባ ቀናት በምድር ላይ የተመላለሰው በትንሳዔ አካል ነው። *‹‹…መቃብሮችም ተከፈቱ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ ከትንሳዔውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ›› ማቴ.27፡52-53*

በዚህም ክፍል የምንመለከተው የተነሱት ሙታን በትንሳኤው አካል እንደሆነና ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ነው።

ክርስቶስ በምድር ላይ ንጉሥ ሆኖ በሚገዛበት ግዛት (Millennium) በምድር ላይ ሊኖሩ እንደማይችሉ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ በእርግጥ የአስቆሮቱ ይሁዳ ለሦስት ዓመታት ከኢየሱስ ጋር አብሮ ኖሮ ሸጦታል፤ ፈሪሳውያን ደግሞ የክርስቶስን ድንቆች እያዩ ባለማመን የአይሁድን ሕዝብ በእርሱ ላይ





እንዲነሳና እንዲሞት ለማድረግ ከማነሳሳት አልተመለሱም። በተጨማሪም ከደቀመዛሙርቱ እንዳንዱ ክርስቶስ በትንሳኤ አካል ሲገለጥላቸው ተጠራጥረው ነበር *ማቴ.28፡17* በክርስቶስ ፊት እንዲህ ዓይነት የልብ ድንዳኔ ሲኖር ለማመን ያስቸግራል። ነገር ግን ሰይጣን ራሱ ከተከበረበት ከእግዚአብሔር ሕልውና ከላይ ከሰማይ ክብሩን ማጣቱና መጣሉ ሊታወስ ይገባል።

## 18.3 የሺህ ዓመት መንግሥት ውበትና ድንቅ ውጤት

በሺህ ዓመት መንግሥት ጊዜ ሰዎች ወደ ክርስቶስ አይመጡም ማለት ሳይሆን ከተለያዩ የሕብረተሰቡ ክፍሎች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የእግዚአብሔር ህልውናና ፈጣሪነት ከልባቸው የማያምኑ ዓለም በድንገት ወይም በአዝጋሚ ለውጥ (evolution) እንዳመጣ የሚቆጠሩ ሰዎች እንዳሉ የሚጠረጠር አይደለም። በተመሳሳይ አመጽና ክፋት እጅግ እየበዛ መምጣቱም ጊዜው ውስብስብና ያልተረጋጋ እንዲሆን አድርጎታል።

ከእግዚአብሔር ለሺህ ዓመት መንግሥት ለ(Millennium) መልካም ነገር ስናስብ አሁን በጉልህ ላይታየን ይችላል። ቢሆንም በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ የአስተዳደር መዋቀር አመራርና በቤተሰብ ዙሪያ የሚከሰቱ ለውጦች እንደሚኖሩ ይታዩናል። በቤተ ክርስቲያን ዘመን ደግሞ በግለሰቦችና በሌሎችም ጌታን በሚያምኑ ላይ የሚሆንን ሰማያዊና ምድራዊ በረከት የእግዚአብሔር ዓላማ እንደሆነ ተብራርቷል። በአሁኑ ጊዜ መጠነኛ የሆኑ ለውጦች እየታዩ ቢሆንም የመንፈሳዊ መነቃቃት ጊዜ ሲመጣ ደግሞ በሕብረተሰቡ ላይ በቤተሰብና እንዲሁም በየድርጅቱና በመንግሥት አሠራር ላይ ተፅዕኖ አይኖረውም አይባልም። በሺህ ዓመት መንግሥት በግለሰቦች በየ

መዋቀሩ ላይ የእግዚአብሔር ጥበብ የሚገለፅበት ሲሆን በውበቱም ጎልቶ ይወጣል።

በተጨማሪም የሺህ ዓመት መንግሥት (Millennium) የእግዚአብሔር የጽድቅ ሥራ ይታያል። ኃጢአተኞችና አመጸኞች ቢኖሩም እንኳን ከአካባቢ ሁኔታ ውጪ በሚሆን ክፋትና ተፅዕኖ ሳይሆን ከሰዎች የውስጥና የልብ ክፋት እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ ከማመጽ መነሻ የሚከሰት ክፋት ነው። ስለሆነም የእግዚአብሔር የጽድቅ ፍርድ ሙሉ በሙሉ በመጨረሻው የፍርድ ቀን ይጠብቃቸዋል። ለሺህ ዓመት መንግሥት ሰይጣን ታስሮም ሰዎች ኃጢአት ከመሥራት አለመመለሳቸው ኃጢአት በሰይጣን ተፅዕኖ ብቻ ሳይሆን በሰዎች ልብ ስር የሰደደ መሆኑን እንገነዘባለን።

## 18.4 የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ለህዝቡ

በአጠቃላይ የመፅሐፍ ቅዱስ ሚዛናዊ ሁኔታ ሲታይ እግዚአብሔር የዘላለም ዕቅዱንና ሀሳቡን ዕለት ዕለት የሚገልጠውና ቃሉን ለመፈጸም የሚተጋው ለሰዎችም ካለው ፍቅርና ርኅራኄ መነሻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የማይታጠፍና የሚፈጸም ነውና።

ከአብርሃም መጠራት ጀምሮ እስከ ይስሐቅ መወለድ ከዚያም እስከ ያዕቆብና ወደ ግብፅ ከመጓዝ ጀምሮ በግብፅ ሀገር የእግዚአብሔር ህዝብ ኑሮና ከዚያም ወደ ከንዓን ጉዞ ስንመለከት አስደናቂ የሆነ የተስፋ ቃል ሲፈጸም ይታያል። በቃል ኪዳኑ መሠረትም የህዝቡ አንድነት በአንድ መሪ በሙሴ አማካይነት ከግብፅ ምድር በእግዚአብሔር ተአምራዊ አመራር ሲወጡና በተስፋይቱ ምድር ሲሰፍሩ እናያለን። የዳዊት መንግሥት የሰሜንና የደቡብ መከፈል የባቢሎን ምርኮና ከምርኮ መልስ





የቤተ መቅደስ መገንባት፣ ታማኝ የሆኑ የህዝቡ ቅሬታዎች መትረፍና በመጨረሻም የኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መምጣት (መወለድ) ስንመለከት የእግዚአብሔር አስደናቂ ዕቅድ እየጨመረና እየደመቀ መምጣቱን ያሳያል። በኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ለሰላሣ ሦስት ዓመት በስጋ መመላለሱ ራሱ እየጨመረ የመጣውን የእግዚአብሔር ክብርና ግርማ የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት፣ በእርሱም ከሞት መነሳት (ትንሳኤ) እና ወደ ሰማይ ማረግ እንዲሁም የእኛን የደህንነት ሥራ መፈጸሙ ከዚሁ ከእግዚአብሔር የዘላለም ዕቅድ ጋር የተያያዘ ነው።

ዛሬ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ መስራጨትና መስፋፋት እንደቀጠለ ቢሆንም በርካታ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ወንጌል ሰምተው ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያልተመለሱ እንዳሉ ስንረዳ ወንጌል ለሁሉም የሚደርሰው መቼ እንደሆነ በውል ሳንረዳ እንቸገራለን። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር የዘላለም እቅድና መልካም የማይታጠፍና በሂደት መፈጸሙ የማይቀር ነው። ክርስቲያኖችም በዘመናቸው ክርስቶስን ወደ መምሰል ህይወት ቢያድጉና በየዕለቱ በጸጋው ጉልበት ከእርሱ ጋር ህብረት በመፍጥር እድገትን እያሳዩ መሄድ እንዳለባቸው ያስረዳል። ስለሆነም እግዚአብሔር በማይታበልና በማይታጠፍ የተስፋ ቃል ኪዳኑ አስደናቂ ከሆነው ከዘላለም መንግሥት ግዛት በፊት ይህንን የሺህ ዓመት መንግሥት ጊዜ አዘጋጅቷል። ስለሆነም ይህንን ሁኔታ መሳዕከቱም በአድናቆት ለማየት ይናፍቃሉ ይመኛሉም።

## ክፍል አስራ ዘጠኝ

# የድህረ ሺህ ዓመት አስተሳሰብ

## 19.1 የድህረ ሺህ ዓመት መንግሥት (postmillennials)

### የመከራከሪያ ሀሳቦች

የድህረ ሺህ ዓመት መንግሥት መከራከሪያ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

የታላቁ ተልዕኮ ዓላማ ወንጌል ወደ ፊት መሄዱንና በከፍተኛ ደረጃ ዓለም ወደ ክርስትና እምነት እንደሚያመራ ይህንንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ *በማቴ.28:18-20 «...ሥልጣን በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፡፡ እንግዲህ ሂዱና አህዛብ ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ»* ያለውን በመጥቀስ ታላቁን ተልዕኮ ለመፈጸም የምንችለው ክርስቶስ ራሱ በገባው ቃልኪዳን መሠረት ከእኛ ጋር ከመሆኑ የተነሳ ያለምንም ክልካይ ሥራው እንደሚጠናቀቅ ነው፡፡

በሰናፍጭ ቅንጣት የተመሰለችው የእግዚአብሔር መንግሥት ቀስ በቀስ ወደከፍተኛ ደረጃ የማደግዋ ሁኔታም ከዚሁ ጋር የሚያያዝ ሂደት ነው፡፡ ይህች የሰናፍጭ ቅንጣት ፍሬዋ ትንሽ ሆና በመሬት ላይ ከተዘራች በኋላ አድጋ ትልቅ እንደምትሆን እንዲህሲል ጌታ በምሳሌ ነገራቸው፡፡

*«...መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች እርስዋም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፤ በአደገች ጊዜ ግን ከአትክልቶች ትበልጣለች...»* ማቴ.13:31-32 የሚለውንና ሌላም ስለ መንግሥተ ሰማያት ጌታ የተናገረውን ምሳሌ እንደማስረጃ በመጠቀም እነዚህ ምሳሌዎች የሚያመለክቱት ይህ የሺህ ዓመት መንግሥት እያደገ ሄዶ ዓለምን በሙሉ እንደሚያጠቃልል የሚያቀርብ ሀሳብ ነው ይላሉ፡፡ እነዚህ ድህረ ሺህ ዓመት መንግሥት ሀሳብ አራማጆች ሌላው የሚያቀርቡት መከራከሪያ ነጥብ ዓለም በሙሉ ክርስቲያን እየሆነ ነው የሚል ሲሆን ቤተ ክርስቲያንም እያደገችና እየተስፋፋች ሲሆን ምንም እንኳን ስደትና መከራ ቢደረስባትም እድገቷ በእግዚአብሔር ኃይልና ጉልበት እገዛ ሥራዋ ቀጥሏል ይላሉ፡፡ በመሠረተ ሀሳቡ ሁሉም በአንድ ርዕስ ሲከራከሩ ቅድመ ሺህ ዓመት አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስ በታደሰች ምድር በትንሳኤ አካል ከተለወጡ ምዕመናን ጋር በጉልህ በሥጋ ለሺህ ዓመት እንደ ሚነግሥ ሲያምኑ ድህረ ሺህ ዓመት አማኞች ደግሞ የሚሉት በምድር ላይ በጣም ብዙ አማኞች በሌሎች የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩበት ጊዜ ነው ይላሉ እንጂ ስለ ምድር መታደስ ስለ አማኞች በቱለወጠ የትንሳኤ አካል መገለጥ ወይም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ ከከበሩ ምዕመናን ጋር ምድርን ስለ መግዛቱ አያወሱም፡፡ እነርሱ የሚሉት ይህ የሚሆነው ክርስቶስ ዳግም ሲመለስ በዘላለሙ መንግሥት ግዛት ወቅት ብቻ ነው የሚል ሀሳብ ነው፡፡ ቢሆንም የሺህ ዓመት መንግሥት (Millennium) እንዲሁ በዘፈቀደ የሚደረግ የምሁራን መከራከሪያ ሀሳብ ሳይሆን ከጊዜና ከሁኔታ ሁሉ በላይ ሊታሰብበት የሚገባ ወቅት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በተለይም የተፈጥሮ ክስተትና የተለያዩ ሁኔታዎች ከምናየውና ከምንሰማው ሁሉ ልዩ ጊዜ እንደሚያስከትል መገንዘብም ተገቢ ይሆናል፡፡

በአንድ ጊዜ ግን ቅድመ ሺህ ዓመት መንግሥት አማኝና ድህረ ሺህ ዓመት መንግሥት አማኝ መሆን እንዳይቻልም ስለ ሚሊኒየም ሁለቱም ያላቸው ሀሳብ ልዩ ልዩ ነው፡፡

አንድ ሰው ወንጌል በዓለም ሁሉ ከተሰበከና ብዙ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ተመልሰ በቃሉ እንደ ተፃፈው በክበሩና በትንሳኤ አካል ከሞት ከተነሱ ምዕመናን ጋር መንግሥቱን በምድር ይመሰርታል ብለው የሚያምኑ ድህረ ሺህ ዓመት መንግሥት (postmillennialism) ሲሆኑ በሌላ ወገን ደግሞ ቅድመ ሺህ ዓመት መንግሥት አማኞች (premillennialism) ያሁኑን ጊዜ የክርስቲያኖች ቁጥር ብዛት በማየት የድህረ ሺህ ዓመት መንግሥት አማኞችን (postmillennialism) አይደግፋዋቸውም።

## 19.2 የድህረ ሺህ ዓመት (postmillennialism)

### አስተሳሰብ

ታላቁ ተልዕኮ እንደሚናገረው በሰማይና በምድር ያለው ሥልጣን ለክርስቶስ ኢየሱስ መሰጠቱ የእግዚአብሔርን የማይመጠን ጉልበትና የኃይሉን ብርታት ማንም የማይክደው ቢሆንም የብዙዎች ወደ ክርስትና የመመለስ ሁኔታን ክርስቶስ ራሱ እንደሚጠቀምበት አይገልፅም። ምናልባት ክርስቶስ ሙሉ ስልጣኑንና ኃይሉን ተጠቅሞ ዛሬ ብዙዎች ወደ ክርስትና እንዲመጡ እየተደረገ ነው ብለን ብንገምትም ከግምት ያለፈ በታላቁ ተልዕኮም ሆነ በቃሉ ላይ በዚህ መልኩ የተጻፈ ክፍል የለም።

ስለ ሰናፍንጭ ቅንጣትም ሆነ ስለ እርሾ የተጻፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም ምሳሌ ቢሆን የእግዚአብሔር መንግሥት ቀስ በቀስ ከትንሽ ወደ ትልቅ እያደገች እንደምትሄድ ይገልጽልናል። ይሁን እንጂ በምን ያህል መጠን አድጋ የት እንደምትደርስ በጉልህ የተጠቀሰ ነገር የለም። የተጠቀሰውም ምሳሌ እንዲሁ ከመጠን በላይ ተጨንቆ በህብረተሰቡ ላይ ሊያስከትል ይችላል የሚባለውን ማላምት ያቀርባል።





ሌላው ደግሞ ዓለም በሙሉ ክርስቲያን ይሆናል የሚለውን መንደርደሪያ ሀሳብ ሲያቀርቡ በተቃራኒው በአሁኑ ጊዜ ዓለም በክፋት እየባሰች እየሄደች ነው። የሰዎች የሞራል አቋም መንፈሳዊ ሕይወትና ማህበራዊ ግንኙነት እየወረደ የመጣበት ዘመን እንደ ዛሬው ጊዜ እንደሌለ የታሪክና የሥነመለኮት ምሁራንም ማረጋገጫ ይሰጣሉ። በአንፃሩ ደግሞ ዘማዊነትና ለዘብተኝነት (liberalism) በምዕራቡ ዓለም አካባቢ እየበዛ ከመሄዱም በላይ ወደ መንፈሳዊነት መመለሰሱና መሻሻሉ ቀርቶ የሞራል ውድቀት አደናዛዥ ዕፅ (drug)፣ የጋብቻ ሁኔታ ውድቀት፣ ግብረሰዶም፣ ሙስና፣ ውንብድና፣ በባለስልጣናት ላይ አመፅ (አብዮት)፣ ሰርኩሳን መናፍስት መገዛት (መዳፍ አንባቢ፣ የኮከብ ቆጣሪ፣ ጠጠር ጣይ፣ የባህል መድኃኒት ቀማሚ፣ መፅሐፍ ገላጭ ወዘተ. .) እየተባለና የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (new age movement) በተጨማሪም ስግብግብነት፣ ውሸት (ሐሰት)፣ ክህደትና ሌብነት የበዛ ሲሆን ክርስቲያኑ ሕብረተሰብ ራሱም ከእግዚአብሔር ጋር የጠለቀ ግንኙነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

በመፅሐፍ ቅዱስ አማኞች ቦታ ሆነን ስንመለከት እንደ ሺህ ዓመት መንግሥት (Millennium) ግዛት የሚሆን ምድራዊ የሰላም መንግሥት ሊከሰት እንደማይችል ይታወቃል። በአሁኑ ጊዜ ያለው የቤተ ክርስቲያን እድገትና የክርስቲያኖች መብዛት ከአጠቃላይ የዓለም ህዝብ ቁጥር ጋር ሲነፃፀር ሁኔታው ብዙ ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም። ምናልባት ይህ ቁጥር በጣም እበዛ ቢሄድ ለድህረ ሺህ ዓመት መንግሥት ተከታዮች የልብ ልብ ሊሰጣቸው ይችል ይሆናል። ነገር ግን ከንዋኔዎቹ በ (amillennialism) ወይም (premillennialism) የእምነት ሂደት ውስጥ ሊካተቱ ይችሉ ይሆናል። እነዚህም ቢሆኑ ሊመዘኑ የሚገባቸው በመጽሐፍ ቅዱስ በተፃፈው መሠረት በተገቢውና በትክክለኛው ቃል እንጂ በሰዎች ግምት ላይ መሆን የለበትም።

በመጨረሻም ከላይ የተጠቀሰውን ድህረ ሺህ ዓመት (postmillennialism) አስተሳሰብ የሚቃወሙ በርካታ የአዲስ ኪዳን ክፍሎችና ጥቅሶች ያሉ ሲሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው *‹‹በጠበበው ደጅ ግቡ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው›› ማቴ.7:13-14*

ይህ እንግዲህ አብዛኛው ህዝብ ክርስቲያን ይሆናል የሚለውን የሚቃረን ሀሳብ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ክፍል ውስጥ ሲናገር ወደ ዘላለም ጥፋት የሚሄዱና ሰፊውን መንገድ የመረጡ ብዙዎች እንደሆኑና በጠባቡ መንገድ ሲሄዱ የወሰኑት ደግሞ ጥቂቶች እንደሆኑ አስረድቷል፡፡ በተመሳሳይም *‹‹የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?›› ሉቃ.18:8፣* ብሎ ጥያቄ ያቀረበው ምድር በምዕመናን (ክርስቲያኖች) ትሞላለች ማለቱ ሳይሆን በተቃራኒው ግን እምነት መጥፋቱንና ከሃዲዎች መብዛታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

እንዲሁም በተጠቀሰው የእምነት አመለካከት ተቃራኒ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ *2ኛተሰ.2:3-4* ሲናገር ክርስቶስ ዳግም ከመመለሱ በፊት አመፅና ክፋት እንደሚበዛና የአመፅ ሰው እንደሚገለጥ እርሱም የጥፋት ልጅ ሆኖ አዋጅ እየተናገረ በቤተ መቅደስ ውስጥ መቀመጫውን እንደሚያደርግና አምላክ ነኝ ብሎ እነደሚነሳ ይገልጻል፡፡

ለጢሞቴዎስም ስለ መጨረሻው ቀን ሲፅፍለት (*2ኛጢ.ሞ.3:1-5)* በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንደሚመጣ ይህን እወቅ፤ ሰዎች እራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና ገንዘብን የሚወዱ ትምክህተኞች ትዕቢተኞች ተሳዳቢዎች ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ የማያመሰግኑ ቅድስና የሌላቸው ፍቅር የሌላቸው እርቅን የማይሰሙ ሀሜተኞች እራሳቸውን የማይገዙ ጨካኞች ይሆናሉ ይላል፡፡





**ክፍል ሃያ**

# መፅሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ

# ስለ ሺህ ዓመት መንግሥት (Millennium)

ከዚህ በላይ ባሉት ክፍሎች የተጠቀሰው ዝርዝር ሁኔታ የሚያስረዳው ዓለም በጠቅላላው ክርስቲያን መሆንዋን ሳይሆን በዓለም ላይ ሊሆን ያለውን የአመጽና የመከራ እንዲሁም የሰዎችን የልብና የተግባር ክፋት የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም አብዛኛው ህዝብ የክርስቶስን ምጽአት ደስ ብሎት ‹‹ጌታ እንኳን ደህና መጣህ!›› የሚል ሳይሆን *ማቴ.24:30* በተጠቀሰው መሠረት የምድር ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ ስለሚል *ማቴ.24* ስለድህረ ሺህ ዓመት (postmillennialism) እንዲህ ከባድና የማይመለስ ጥያቄ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም ስለመጨረሻው የመከራ ዘመን የሚናገር ክፍል ነው፡፡

በድህረ ሺህ ዓመት (postmillennialism) አመለካከትና አስተሳሰብ የማይገጥሙ ክስተቶች ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት ይፈጸማሉ ከሚባሉት መካከል ተፈፅመዋል የሚሉት በ70ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የኢየሩሳሌምን ከተማ መደምሰስ እንደ አንድ ምሳሌ ይወስዳል፡፡

ይህንን አተረጓጎም ለማፅናት የዚህ እምነት ተከታዮች በተለይ *ማቴ24:29-31* ያለው ምሳሌያዊ አባባል ነው ይላሉ፡፡ ይህንንም ሲሉ የፀሐይና የጨረቃ መጨለም የከዋክብት ከሰማይ መውደቅ (የዩኒቨርስ) መናወጥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመግለፅ

የተጻፈ ስለ ሆነ አባባል ብቻ ነው እንጂ በተግባር የሚፈፀም አይደለም ይላሉ። በተመሳሳይ *በሕዝቅኤል 32፡7፣ ኢዩኤል 2፡10* እንዲሁም *አሞጽ 8፡9* የተጠቀሰው ግምታዊና ምሳሌያዊ አነጋገር ነው ብለው ይደመድማሉ። ነገር ግን እነዚህ ክፍሎች የሚናገሩት በቀጥታ ስለ ጨለማው ፍርድ እንጂ ስለ ከዋክብትም ሆነ ስለ ሰማይ ኃይላት መናወጥ አይደለም። *በኢሳይያስ.13፡10፣ 34፡4* የተጠቀሰው ክፍልም ስለ ፀሐይና ጨረቃ መጨለም እንዲሁም ስለ ሰማይ ኃይላት መናወጥ ይገልጻል እንጂ ከአንዳንድ ግለሰቦች አስተሳሰብ እጅግ የተለየ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *ማቴ.24፡30* ስለ ፀሐይና ጨረቃ እንዲሁን ስለከዋክብት ሁኔታ ሳይሆን *«...ወዲያው በድንገት የሰው ልጅ በደመና በኃይልና በሥልጣን ይገለጣል የምድር ወገኖች ሁሉ የወጉትም ያዩታል...»* የሚለው ሌላ ሁኔታ ሳይሆን በግልፅ እንደተጠቀሰው ክርስቶስ በግርማው ኃይልና ሥልጣን ዳግም እንደሚመለስ ያሳያል እንጂ ምሳሌያዊ አባባል ብቻ ሆኖ አይታይም። በሌላ ስፍራ ጌታ ኢየሱስ የሰው ልጅ ከሰማይ ወደ ምድር በደመናት ይገለጣል ሲል ወደ እግዚአብሔር አብ መውጣቱን ሳይሆን ወደ ምድር ወደ ሰዎች መምጣቱን የሚያሳይ ክፍል ነው።

*ራዕይ.1፡7-8 «...እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል ዓይንም ሁሉ የወጉትም ሁሉ ያዩታል የምድር ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን አሜን። ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል»* ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ክርስቶስ በሚመጣበትን ጊዜ ሊሆን ያለውን ሁኔታ ሲገልጽ *«በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉትን አንቀድምም ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም ዓለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና በክርስቶስ የሞቱት አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን» 1ተሰ.4፡15-17*





ክርስቶስ ኢየሱስ በክብር ደመና በኃይል የሚመጣው በምድር ላይ ሊነግሥ ሲሆን *ማቴ.24፡30-31* ባለው ቃል መሠረት በዳግም ምጽአቱ ወቅት የሚከሰቱት የምድር ምልክቶችና የሰማይ ድንቆች እንዲሁም በደመና መመለሱ የመለከት መነፋት የመላዕክት አጀብ ወዘተ... ምሳሌያዊ አባባል ሳይሆን በተግባር የሚፈፀም እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በእንክሮ ይገልጻል። ከዚሁ ጋር ከላይ በተጠቀሰው *ማቴ.24* ላይ ስለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምልክቶች ከታላቁ መከራ በኋላ ወዲያው የሚከስቱ እንጂ ከሰላምና ክጽድቅ ዘግይቶ የሚሆን የሺህ ዓመት መንግሥት (millennium) በምድር ላይ የሚሆን አይደለም።

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማንኛውም ጊዜ በድንገት ሊመጣ ይችላልና በጥንቃቄ ተዘጋጅተን ልንጠብቅ ይገባናል።







ክፍል ሃያ አንድ

# ቅድመ ሺህ ዓመት መንግሥት(Premillennium) ከሌሎች የሚለይባቸው ባህሪያት

## 21.1 የዘመኑ ልዩ መሆንና የትኩረት አቅጣጫ

የቅድመ ሺህ ዓመት (premillennium) አመለካከት ከተቀሩት ከሁለቱ አመለካከቶች የሚለይባቸዉ የራሱ የሆነ የትኩረት አቅጣጫ ስለያዘ ነዉ፡፡ ይህን በተመለከተ ብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች የሺህ ዓመት መንግሥት በዚህ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ወይም በዘላለሙ ግዛት ወቅት እንደሆነ አይገልጹም፡፡ ይኹን እንጂ በኋለኛዉ ዘመን ሊሆን ያለዉን ሁኔታ ከመጠቆም በስተቀር አመጽ ከሰዎች ባህሪይ መወገዱን ወይም ሞት በምድር ላይ አለመኖሩን አያሳዩም፡፡

ኢሳይያስ ስለሚመጣዉ ዘመን *በምዕ.65፡20* ሲናገር *‹‹ከዚያም ወዲያ ጥቂት ዘመን ብቻ የሚኖር ሕፃን ወይም ዕድሜዉን ያልፈጸመ ሽማግሌ አይገኝም፡፡ ጎልማሳዉ የመቶ ዓመት ሆኖት ይሞታልና ኃጢአተኛዉም የመቶ ዓመት ሆኖት የተረገመ ይሆናል››* ይላል፡፡

የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ራዕይና ትንቢታዊ አነጋገር ባህሪይ ስንመለከተዉ የሁኔታዎቹ (የክስተቶቹ) አፈጻጸም ወይም ክንዋኔ በሁለቱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጫ ወቅቶች በተብራራ መልኩ ተገልጸዋል፡፡

አቀራረቡ በጥቅሉ ሲገለጽ ሁኔታው የተደባለቀ ይመስላል እንጂ በዚህ ክፍል ብቻ የተጠቀሰዉ የህፃናትና

ኪዳን የሰባው ሱባዔና የሺው ዓመት ቅዱሳን ተብለው ይታወቃሉ።

በሺው ዓመት ማብቂያ ላይ ለአጭር ጊዜ ከእስራት የተፈታው ዲያቢሎስ ሰዎችን ለማሳትና ለማሳመፅ አስተባብሮ ለጦርነት ፊልሚያ እንዲዘጋጁ ወደ ምድር ሁሉ ይወጣል። ከምድር ዙሪያ ጎግና ማጎግ በመባል የሚታወቁትን የጦር ሠራዊት አሰልፎ በቅዱሳን ሰፈርና በተወደደችው ከተማ ላይ ለውጊያ ያስከትታል። *ራዕይ.20:8* እነዚህ ሰዎች የሺው ዓመት መንግሥት የመጀመሪያ ዜጎች ልጆችና የልጅ ልጆች ናቸው። የእነዚህ ወደ ሺው ዓመት መንግሥት የገቡት ቅዱሳን ልጆች በጽድቅ መንግሥት ውስጥ የተወለዱ ቢሆኑም በግላቸው ባላቸው ነፃ ምርጫ በጌታ ባልመታመናቸው ምክንያት ሰይጣን በተፈታበት ወቅት ለሸንገላው ምቹ ሆነው የሚገኙት ናቸው። በጌታ የጸኑ ያመኑና የፅድቅ ኑሮአቸውን የቀጠሉ ወደ ሚቀጥለው የዘላለም ሕይወት ሲሻገሩ አመጸኞቹን ግን እሳት ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዶ ይበላቸዋል፣ *ራዕይ.20:9* ያሳታቸው ዲያቢሉስም ተይዞ ለመጨረሻ ጊዜ በእሳት ባህር ውስጥ ይጣላል፤ በዚያም ለዘላለም ይሰቃያል። *ራዕይ.20:10*

## 23.3 የሙታን ትንሳዔ ወቅት

ከፍ ብሎ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ሙታን በሺው ዓመት ፍፃሜ ላይ ይነሳሉ። ይህም የመጀመሪያው ትንሳዔ ከተከናወነ ከአንድ ሺህ ዓመት በኋላ መሆኑ ነው። *ራዕይ.20:5* የዚህ የመጨረሻው ትንሳዔ ተካፋዮች ሰው በምድር ላይ ከተፈጠረ ጀምሮ ለእግዚአብሔር ያልታዘዙና ያላመኑበት እንዲሁም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በንስሐ ለመታደስ





ዳግም ለመወለድ ፈቃደኞች ያልነበሩ በዚህም ምክንያት ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተፃፈ ሙታን ሁሉ ናቸው። *ራዕይ.20:13-15*

ይህም ትንሳኤ

- ❖ የእፍረትና የዘላለም ጉስቁልና ትንሳኤ *ዳን.12:2*
- ❖ የፍርድ ትንሳኤ *ራዕይ.5:29*
- ❖ የኋለኛው ትንሳኤ *ራዕይ.20:29* በመባል ይታወቃል

ይህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን አብቅቶ ቤተ ክርስቲያን ስትነጠቅ ተቋርጦ የነበረው የዳንኤል 70ኛው ሱባዔ እንደገና ይቀጥላል። በዚህ የመጨረሻ ሱባዔ ወይም ሰባት ዓመት ጊዜ ውስጥ የእግዚአብሔር እቅድ ትኩረት እንደገና በእስራኤል ይሆናል። ይህም በሚቀጥለው ክፍል ሰፋ ባለ ሁኔታ ይገለጻል።





## ክፍል ሃያ አምስት

# የክርስቶስ ተቃዋሚ

## 25.1 የክርስቶስ ተቃዋሚ ይፋ መውጣት

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው በዳንኤል ትንቢት በተገለጸው መሠረት 69ኛው ሱባኤ የተፈጸመው ጌታ ኢየሱስ ሲገደል ነው። የቀረውና በመካከሉ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ጣልቃ ስለገባ የተቋረጠው 70ኛው ሱባኤ ወይም ሰባት ዓመት የሚጀምረው በክርስቶስ ተቃዋሚውና በእስራኤል መንግሥት መካከል የሚደረገው ፅኑ ቃልኪዳን ነው። *ዳን.9:27* ይህ ቃል ኪዳን ለእስራኤል አንዳንድ፣ መብቶችን እንደሚያስገኝላት ይታመናል። ከነዚህም መብቶች መካከል ዋነኛው ቤተ መቅደሷን መሥራትና በዚያም እንደቀድሞ፣ የብሉይ ኪዳን ስርዓቷ መስዋትንና ቁርባንን ማቅረብና ሌሎች የመቅደስ ስርዓቶችንም የሚያጠቃልል ነው። *ዳን.9:27፤ ማቴ.24:15፤ 2ተሰ.2:4*

## 25.2 ቃል ኪዳኑን ማፍረሱ

የክርስቶስ ተቃዋሚ የተባለው ለአንድ ሱባኤ የገባውን ቃል ኪዳን በሱባኤው እኩሌታ ማለት በሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ ያፈርሳል *ዳን.9:27፤ ራዕይ.13:5፤ «እርሱም ፅኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባኤ ያደርጋል በሱባዔውም እኩሌታ መስዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል። በርኩሰትም ጫፍ ላይ አጥፊው ይቀመጣል፤ እስከተቆረጠውም ፍፃሜ ድረስ መቅሰፍት በአጥፊው ላይ ይፈሰሳል»*

●

ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚ ሰይጣናዊ ተአምሮችን ማድረግ ይጀምራል፡፡ ራሱም ከሞተ በኂላ በሕይወት ይገኛል፡፡ *ራዕይ.13:3፤ 14:17፤ 2ተሰ.2:9* ዲያቢሉስ ኃይሉን ዙፋኑንና ትልቅ ሥልጣን ይሰጠዋል *ራዕይ.13:2፤* ከአማልክት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ በማድረግ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይቀመጣል፡፡ *ዳን.11:36፤ ማቴ24:15፤ 2ተሰ.2:4፤ «ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ ግን ራሱን ከፍ ከፍ ያደረገውን ተቃዋሚ በአፉ እስትንፋስ ያጠፋዋል»2ተሰ.2:8፤ራዕይ.19:21*

## 25.3 የሐሰተኛው ክርስቶስ ህዝብን ማስገድ እና "666"

የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሲያበቃ ቤተ ክርስቲያንና እውነተኛ ክርስቲያኖች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ወደ ሰማይ በተነጠቁበት በሰባኛው ሱባኤ ውስጥ የዓለምን ታሪክ ትኩረት የሚስበው ሌላው ሰው ሐሰተኛው ነብይ ተብሉ የሚታወቀው ሰው ነው፡፡ *ራዕይ.13:11*

ይህም ሐሰተኛው ነብይ

- በሐሰተኛው ክርስቶስ ሥልጣን ይሠራል፡፡ *ራዕይ.13:12*
- በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ለክርስቶስ ተቃዋሚ እንዲስገዱለት ያደርጋል፡፡ *ራዕይ.13:12*
- እሳትን ከሰማይ እስከማውረድ ድረስ ያሉትን ተአምራቶች ያደርጋል፡፡ *ራዕይ.13:13*
- ለክርስቶስ ተቃዋሚ ምስል እንዲሠሩ ህዝብን ያነሳሳል፡፡ የተሠራውንም ምስል እስትንፋስ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ *ራዕይ.13:15*





- ሰዎች ሁሉ የክርስቶስን ተቃዋሚ ስም ወይም የስሙን ቁጥር በክንዳቸው ወይም በግንባራቸው እንዲቀበሉ ያስገድዳል ካልተቀበሉ መግዛት ወይም መሸጥና መገበያየት እንዳይችሉ ያደርጋል፡፡ ቁጥሩም የሰው ቁጥር ነው የተባለው ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት (666) ነው፡፡

ይኸን እንጂ የክርስቶስ ተቃዋሚና ሐሰተኛው ነቢይ የተባሉት ወደ ገሃነም እሳት ለመጣል የመጀመሪያዎቹ ፍጡራን እንደሚሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል፡፡ *ራዕይ.19:20* እነርሱ ዲያቢሉስ ተፈርዶበት ከመጣሉ ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት ስለሚጣሉ በገሀነም በመጣል ዲያቢሉስን በአንድ ሺህ ዓመት ይቀድሙታል፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን የፅድቅ ፍርድ ተግባራዊነት የሚያሳይ ሂደት ነው፡፡

ለማስተባበል በኦክቶበር 1,1914 ወደ ምድር መጥቶአል ማለት ጀመሩ። በቅርቡ በ20ኛው ክፍለ ዘመን እ.ኤ.አ 1988 በበጋ ወራት አንድ የታወቀ ምሁር ኢየሱስ ክርስቶስ እ.ኤ.አ ሰፕቴምበር 12,1988 ይመጣል ብሎ በአሜሪካና በመላው ዓለም በመጣጥፎችና በመጽሔቶች ጽፎ በብዛት አሰራጨ። በኋላ ሁኔታው ሳይሆን ሲቀር ስለ ምጽአት ሳሰላ ተሳስቼ ነውና ክርስቶስ የሚመለሰው በዓመቱ ሰፕቴምበር 12, 1989 ነው በማለት ሽንጡን ገትሮ ሌሎችን ለማሳመን ተከራከረ። ሀሳቡም ተቀባይነት እንዲኖረው ሲጥር ቀመሩን ተሳስቼ ይሆናል እንጂ ከዚህ በላይ በተባለው ቀን ባይመለስም ከ1990 ወይም 1991 ከዚያም ቢያልፍ 1992 ይሆናል። ወይም ደግሞ በእነዚህ ጊዜያት ካልመጣ እ.ኤ.አ ሰፕቴምበር 15-17, 1993 ይመጣል ብሏል። ነገር ግን ሁሉም ሳይሆን ቀረ ምክንያቱም የሐሰት ትንበያ ነውና። *‹‹የጌታን መመለሻ ቀን እንዲያውቅ ሥልጣን የተሠጠው ማንም የለም›› ማቴ 24:42-44፤ 50*

በእርግጥ አንዳንድ ጥቅሶች ኢየሱስ ክርስቶስ በማንኛውም ሰዓት በድንገት ይመጣል ሲል ሌላ ቦታ ደግሞ ከእርሱ ዳግም ምጽአት በፊት ስለሚሆኑት ሁኔታዎች ይገልጻል። የሁለተኛው ሀሳብ ከጌታ ምጽአት በፊት በዓለም ላይ ሊሆኑ ያሉትን ምልክቶች፣ የሚሆኑ ድርጊቶችንና ክስተቶችን እንድንጠብቅ የሚያደርግ ስለሆነ ሰዎች ችላ እንዲሉ የሚጋብዝ ይመስላል። ቢሆንም ከፍ ብሎ በተደጋጋሚ በተገለጸው መሠረት ምን ጊዜም ሳንዘናጋ የጌታን ዳግም መምጣት ተጠንቅቀን ልንጠብቅ ይገባናል *ማቴ.25:13፡ ‹‹እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ›› ራዕይ.22:12*

ስለዚህ ማንኛችንም ብንሆን የእግዚአብሔርን ቃል በተሳሳተ ትርጉም ወስደን ጌታ ዛሬ ወይም ነገ ይመጣል በሚል ሥራ መፍታትና መዘናጋት የለብንም። ይልቅስ ነቅተን ‹‹የጌታ ሥራ የበዛላችሁ ሁኑ›› ተብሎ እንደተጻፈ ወደ እግዚአብሔር





በመመለስና ሌሎችንም ከጥፋት በማዳን እንዲሁም የዘወትር ተግባራችንን በጽድቅና በቅድስና እያከናወንን ብንጠበቅ ሥራ ፈቶችና ፍሬቢሶች አንሆንም።

## 26.4 የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ውጤት

በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያምኑ ክርስቲያኖች በሙሉ የውስጥ አመለካከት ልዩነቶች ቢኖሯቸውም ስለ ጌታ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት፣ ስለ መጨረሻው ፍርድ፣ ያላመኑ ስለሚቀጡበት ቅጣትና አማኞች በመንግሥተ ሰማያት ስለሚቀበሉት ሽልማት ያላቸው እምነትና አመለካከት ልዩነት የለውም።

ይህ እንዲህ ከሆነ ጥፋት የሚመጣው ከሌላ ሳይሆን *‹‹ህዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል›› ሆሴ.4:6* በሚለው ቃል መሠረት ቃሉን አለማወቅ መንገዱን አለማወቅ ነው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል *‹‹በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች ዕወቁ በእርሷም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ›› ኤር.6:16* ይላል።

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ለግሉ የሰጠው ነፃ ምርጫ አለው። በዚህ ነፃ ምርጫው መልካሙንና ክፉውን ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን የዘላለም ሕይወትንና የዘላለም ፍርድን ወዘተ... ለይቶ ይጠቅመኛል የሚለውን እንዲመርጥ አእምሮና መንፈስ የተሰጠው ስለሆነ በራሱ ምርጫ ላይ የተመሠረተን የመጨረሻ ፍርድ ይቀበላል።

በመጨረሻው ሰዓት ሐሰተኞች ነቢያት እንደሚነሱ ጌታ ኢየሱስ ሲናገር *‹‹ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳን ያስቱ ዘንድ ምልክትንና ድንቅን ያደርጋሉ›› ማር.13:22*

*ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለእናንተ ይታገሳል»*
*2ጴጥ.3፡9*

ከዚህም ጋር ዓለም የምትጠብቀው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ ሦስት ዓመት ተኩል በፊት የሚመሠረተውን የዓለም መንግሥት ነው፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ስለ እስራኤልና በተለይ ስለ ኢየሩሳሌም የተነገሩ ትንቢቶች የብዙዎችን ትኩረት ሊስቡና የፍፃሜውን ዘመን አቅጣጫ ጠቋሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከተፈጸሙት ትንቢቶች አንዱ አገር የለሽ የአይሁድ ህዝብ ለብዙ ዘመናት ከተበታተነበት ስፍራ ወደተስፋ ምድሩ ተመልሶ መንግሥት መስርቶ መኖሩ በራሱ ተዓምራዊ የትንቢት ፍጻሜ ክስተት ነው፡፡ በመጨረሻ ዘመንም የሚሆነውም እነዚህ እስራኤሎች ዛሬ ባሉበት ሁኔታና ቦታ እንዳሉ እንዲሆን ትንቢቶቹ ይጠቁማሉ፡፡

*በዮሐንስ ራዕይ 17* ላይ የተጠቀሰችውና በብዙ ውሃዎች ማለትም በወገኖችና ብዙ አህዛብም ቋንቋም ላይ የተጠቀሰችው ይህቺ ታላቂቱ ጋለሞታ የጋለሞታዎችና የምድር እርኩሰት እናት የተባለችው ‹‹የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት›› በሚል የምትቋቋም እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡

እነዚህ ክስተቶች በሙሉ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እየተከናወኑ ወደፍጻሜ በመጣደፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመጨረሻም የዓለም አቀፍ ሃይማኖት ድርጅት በአብያተ ክርስቲያናት ስም ለጊዜው እየተደራጀና የማይነቃነቅ መስሎ ቢታይም እውነተኛ ክርስቲያኖች ከተነጠቁ በኋላ እርቃኑን ይቀራል፡፡





## ክፍል ሃያ ሰባት

# የመጨረሻው የጽድቅ ፍርድ

### 27.1 የጋለሞታይቱ የመጨረሻ ፍርድ

- ***ጋለሞታይቱ የተባለችው ቤተ ክርስቲያን (ድርጅት)***

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት ሊገለጡ ካሉት ክስተቶች መካከል አንዱ ታላቂቱ ባቢሎን የሚል የቅጽል ስም የተሰጣት የጋለሞታይቱ መገለጥ ነው፡፡ ይህች ጋለሞታ የምድር ነገሥታት ከእርስዋ ጋር እንዲሴስኑ ያደረገችና በምድር የሚኖሩ ሁሉ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ እንዲሰክሩ ያደረገች እንደሆነች *በራዕይ 17* መገለፅ ከላይ ባለው ክፍል ተብራርቷል፡፡

በተጨማሪም በግንባርዋ ላይ የተጻፈ የሚስጥር ስም ደግሞ ‹‹ታላቂቱ ባቢሎን የጋለሞታዎችና የምድር እርኩሰት እናት›› የሚል ነበር፡፡ ሴቲቱም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ ሰባት ራሶችንና አሥር ቀንዶች ባሉት አውሬ ላይ የበላይ ሆናና አምራ የተቀመጠች እንደሆነ በክፍሉ ተብራርቷል፡፡

ይህ ሲገለጥ ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ራሶች ሰባት ነገሥታት እንደሆኑ ታውቆአል፡፡ ስለሆነም ከላይ እንደገለጸው በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚዋቀረውን የሃይማኖት ድርጅት በበላይነት የምትመራ ዓለማዊት የሆነች ቤተ ክርስቲያን ታላቂቱ ጋለሞታ ተብላ ተሰይማለች፡፡

አንድነትና አሠራሩን እንዲሁም ዓለምን ሊገዛ የሚነሳውን ሐሰተኛውን ክርስቶስና የሁለቱንም የመጨረሻ ጥፋት ሲያሳይ።
2ኛ) ቅድስቲቱን ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በመባል የምትታወቀው ድንግሊቱ የተባለችው ራስዋን ያዘጋጀችው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆንና እርሱ ዳግም ሲመለስም ከእርሱ ጋር ለመንገሥ የተዘጋጀችውን ቤተ ክርስቲያን ወይም እውነተኛ አማኞች የሚያሳይና በጉ የተባለውም የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ የተባለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን እንመለከታለን።

በዓለም ላይ ያለው እያንዳንዱ ሰው ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት የአንዱ አባልና ደጋፊ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ይኹን እንጂ ዛሬ ዓለም በተለየ ሁኔታ ወደ መጨረሻው ዘመን እየገሰገሰች ስለሆነ ያለቸልታ የሕይወትን መንገድ በአስቸኳይ መምረጥ ከነገ ቁጭትና ከዘላለም ፍርድ ያስመልጣል።

## 27.3 ስለ ሺህ ዓመት መንግሥት (millennium) ለቤተ ክርስቲያ የተነገረ ትንቢት

የመጨረሻዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያን በተመለከተ የጊዜን ቅደም ተከተል ስንመለከት አንዳንድ ሰዎች ባይገባቸውም ዓለም ለክርስቶስ ልትገዛ ሁሉ ነገር ግን አለቆ የተዘጋጀች ትመስላለች። ስለሆነም ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለእውነተኛ አማኞች የተነገረ ተስፋ ሊፈጸም መቃረቡ በግልጽ እየታየ ነው። ይኸውም ትንተናው እንደሚከተለው ቀርቦአል፡ -

1. በዓለም ላይ የኮሚኒዝም መነሳትና በይፋ እግዚአብሔር የለም ብሎ መካድ





2. የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጤንነት የመረዘ በአውሮፓና በአሜሪካ የተነሳ ለዘብተኝነት (liberalism)
3. የዓለም አቀፉና የኃያሏ ቤት ክርስቲያን ህብረት (ecumenical movement) መመሥረት
4. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን መቃወም ከሃዲነትና ግብረ ሰዶም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገሃድ መሆን መጀመር
5. ከክርስትና ሥነ ምግባር ፈጽሞ በመራቅ በቤተ ክርስቲያን ቀውስና ችግር መፈጠር
6. የሰይጣን አምልኮንና ጥንቆላን የተማሩ ሰዎችና የሀገር መሪዎች ጭምር መለማመዳቸውና በዚህም ተጽዕኖ ሥር መሆናቸው ዓለምን ለሰይጣን የመጨረሻው ሰዓት በማዘጋጀት ላይ መሆን
7. ኢየሩሳሌም የአይሁድ እምነት፣ ክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እንደ ቅድስት ከተማ የሚመለከቷት ቢሆንም እስካሁን ድረስ ያልበረደ ውዝግብ መኖሩ
8. አይሁዶች ከተማይቱን ማዕከል በማድረግ በቀድሞ የሰለሞን ቤተ መቅደስ አሁን አልአቅሳ የተባለው መስጊድ በተተከለበት የራሳቸው ቤተ መቅደስ ለማቆም ማቀዳቸው
9. ከፍተኛውና ዘግናኙ እልቂት በዓለም ከመፈጸሙ በፊት ቤተ ክርስቲያን ወይም እውነተኛ አማኞች ከክርስቶስ ጋር ለመሆን ከዓለም ተነጥቀው ይሰወራሉ
10. ክፉ አድራጊና ድርጊቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መገታቱ ያበቃል
11. ኃያሏ ቤተ ክርስቲያን የተባለችው የክርስቶስ ተቃዋሚ ሆኖ ለሚነሳው ሰው የዓለም ገዥ እንዲሆን እገዛ

ስታደርግ ዋና ዋና ሃይማኖት በማሰባሰብ ለሐሰተኛ ነቢይ መነሳት እንደመሣሪያ አድርጋ ትጠቀምባቸዋለች

12. የክርስቶስ ተቃዋሚ ኃያሊቱ ቤተ ክርስቲያን የተባለችውን ያፈርስና ራሱ መመለክን የሚፈልግ (አምላክ ነኝ) የሚል ገዥ ይሆናል

13. በሺህ የሚቆጠሩ አማኞች በእምነታቸው ለዘብተኝነትና ባለመዘጋጀታቸው ምክንያት ሳይነጠቁ የቀሩ በዚህ ዘመን እስከሄፊ መከራና በሞት ሰማዕትነት ያልፋሉ በሰባቱ ዓመት መጨረሻ ክርስቶስ በታላቁ መከራ ቀደም ብለው ወደ ሰማይ ከተነጠቁት ክርስቲያኖች ጋር ይመለስና የዓለም መንግሥታትን አገዛዝ በአማርጌዶን ጦርነት እንዲያከትም ያደርጋል።

## 27.4 ስለ ሺህ ዓመት መንግሥት (millennium)

### ለእስራኤላውያን የተነገረ ትንቢትና ሂደቱ

ስለ አይሁድ ሕዝብና መንግሥት የተነገሩ ትንቢቶች ልዩ ትኩረት የሚሰጥባቸው ምክንያት ኢየሩሳሌም የመካከለኛው ምስራቅ የትኩረት ማዕከል ከመሆንዋም በላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለመጨረሻው ዘመን ሲናገሩ አጥብቀው ስላስገነዘቡ ነው።

ምንም እንኳን የሀገሪቱና የሕዝቡ ታሪክ ከሌላው ዓለም ታሪክ ተገንጥሎ ባይታይም ትንቢታዊ ማገናዘቢያዎችና አስደናቂ ክንዋኖች እየተጣደፉ በመፈጸም ላይ መሆናቸው ግልጽ ነው።





ይኸውም: -

1. አይሁዶች በተነገረው ትንቢት መሠረት ከተበታተኑባቸውና ከተሰደዱባቸው ሀገሮች ወደ ፓለስቲና (ፊልስጤኤም) እ.ኤ.አ በ1948 ዓ.ም ተመልሰው መንግሥት መመስረታቸው
2. አዲሲቱን እስራኤል የተለያዩ የዙሪያዋ መንግሥታት የሚሰነዝሩባትን ጥቃት እየመከተች መጽናቷ
3. ሩሲያና ሌሎች አንዳንድ አገሮች የእስራኤል ጠላት ሆነው ሲነሱ አሜሪካ ደግሞ ከእስራኤል ጎን መቆሟ
4. እስራኤል ጠላቶችዋን ተቋቁማ ኃይልዋን በጀግንነት ለማጠናከር መቻልዋና ታዋቂ መንግሥት መሆንዋ
5. የእስራኤል ወታደራዊ ድል ዐረቦች አብዛኛውን የዓለም የነዳጅ ሀብት በመቆጣጠር በሚያደርጉበት ዲፕሎማሲያዊ ፍልሚያ መጋረዱና በአውሮፓና ቁልፍ በሆኑ የዐረብ ሀገሮች መካከል ባለው ጥብቅ ግንኙነት ምክንያትም ዐረቦች ያላቸው ደረጃ ከፍ ማለቱና እያደገ መሄዱ
6. አሜሪካና ሩስያ ከመካከለኛው ምስራቅ ገለልተኛ መሆናቸው እየጨመረ መምጣቱ ለእስራኤል ተቀባይነት ያለው የሰላም ድርድር ለማድረግ ችግር መፈጠሩ
7. ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ እስራኤል በአዲሱ የሜዲትራኒያን የመንግሥት ህብረት መሪ የሚሰጣትን የይስሙላ የሰላም ዋስትና ውል ለመቀበል ትገደዳለች

2. ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የአውሮፓ ህብረት እንደገና መገንባት በወደፊቱና በትንቢት የሮም መንግሥት ተብሎ ለተነገረው ግዛት ተሐድሶ የሚጫወተው ሚና አመቻችቶአል
3. የእስራኤል መንግሥት እንደገና መመሥረቱና በዓለም ላይ ተበታትነው የነበሩት አይሁዶች መሰብሰባቸው
4. ሩሲያ የሚል ስም በመጻሐፍ ቅዱስ ባይጠቀስም በሰሜኑ በኩል ስላሉት ሀገሮች ስለሚናገር ሀገሪቱ በዓለም ኃያል መንግሥት በመሆን የዐረብ ሀገሮች ተባባሪ መሆንዋ
5. የዓለም የጋራ ገበያና የዓለም ባንክ አጠቃላይ የዓለም ኢኮኖሚን በአንድ ማዕከል ለመቆጣጠር እንዲቻል ድንጋጌ የሚያሻ መሆኑን መጠቆማቸው
6. ቻይና በጦር ኃይል በመሣሪያ እንዲሁም በጦር ሠራዊት ወታደራዊ አቅም ኃያል መሆንዋን ማሳየቷ
7. የመካከለኛው ምስራቅ በተይም የዐረቦችና የእስራኤል ውዝግብ በየጊዜው እየጨመረ መሄዱ
8. የነዳጅ ዘይት ዋጋ መናርና የዓለምን የኃይል ሚዛንና የሀብት ክምችት በሜዲትራኒያን አካባቢ እንዲተኩር ማድረጉ
9. ምዕራባውንና ምስራቃውያን ተብለው በሁለት ጎራ ተከፍለው የነበሩት የአውሮፓ ሀገሮች አንድነት መሥርተው በአንድ ገንዘብ (euro) መጠቀማቸው
10. ከፍተኛ የነበረው የሩሲያ ኃያልነት በመካከለኛ ምስራቅ ላይ ያላት ተጽዕኖ ያበቃል





11. የነዳጅ ዘይት ዋጋ በተከታታይ በመናሩ በሽብርተኝነትና በመካከለኛው ምስራቅ በሚፈጠረው ግራ የተጋባ ወታደራዊ ሁኔታ የተነሳ ዓለም ስለ ሰላም የምታሰማው ጩኸትና ዋይታ እየጨመረ መሄዱ
12. አሥር መንግሥታት የሜዲትራኒያንን ህብረት ሲመሠርቱ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው አራተኛውና የመጨረሻው ትንቢታዊ የዓለም መንግሥት ዘመን የሚጀምር መሆኑ
13. አንድ አዲስ የሜዲትራኒያን መሪ ሳይታወቅበት በአስደናቂ ሁኔታ ሥልጣኑን ተጠቅሞ የህብረቱን ሦስት አባል መንግሥታት በማመሰቃቀል በመካከላቸው አለመግባባት እንዲፈጠር በማድረግ የአሥሩን መንግሥታት ህብረት ራሱ ይቆጣጠራል
14. ይህ አዲሱ የሜዲትራኒያን መሪ በመካከላኛው ምስራቅ ‹‹የመጨረሻ›› የሰላም ስምምነት ያደርጋል ስምምነቱ ግን ከሦስት ዓመት ተኩል በኃላ ይፈርሳል
15. የሩሲያ ሠራዊት እስራኤልን ለመውረስ ይሞክርና በተአምር ይወድማል
16. አዲሱ የሜዲትራኒያን መሪ የዓለም አምባገነን ገዥ መሆኑን ያውጃል ከእስራኤል ጋር የነበረውን የሰላም ስምምነት ያፈርሳል ከዚያም *‹‹እኔ አምላክ ነኝ››* ይላል *ራዕ.17፡1-18*
17. ይህ አምባገነን መሪ የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ያረክሳል
18. ታላቁ መከራ ተብሎ የተነገረው አስከፊ ፍዳዎች በዓለም ሕዝቦች ላይ የሚወርዱበት ነው

አቀፋዊ የሆነ ማዕከላዊነት ይኖረዋል *ኢሳ.2:4፤ ሚል.4:3፤* አስተማማኝ ጥበቃ ያለበት ይሆናል *ኢሳ.32:18፤* እስራኤላውያን ጦርነት አብቅቶ በሀገራቸው በሰላም የሚቀመጡበት ነው *አሞ.9:14-15*

5. *የሚታይና የሚጨበጥ ተግባራዊ መንግሥት ነው፡* - ይህ መንግሥት በግልጥ በምድር ላይ የሚሆን ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የመንግሥቱ ባህሪያት መንፈሳዊ ናቸው ሲባል በመንፈሳዊ ዓለም የሆነ ነው ማለት ግን እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፡፡ ስለዚህ ከተፈጥሮ ሁኔታ የተለየ ሳይሆን የታመመና በሽተኛ የሆነ ተፈጥሮ የሚፈወስበት መንግሥት ነው ለማለት ነው *ኢሳ.32:24-35፤ 5-6፤* ረዥም ዕድሜ መቆየት የሚቻልበት *ኢሳ.65:2፤* የተፈጥሮ ችግርና መከራ የሚወገድበት ነው *ኢሳ.65:32፤ ሕዝ.34:23-31፤* የምድሪቱ ልምላሜና አጠቃላይ ሁኔታ (geological) ለውጥ የሚታይበት ይሆናል ዘካ.14:3-4፤ የአየር ለውጥ ማለት ለሁሉም ተስማሚ ይሆናል *ኢሳ.32: 15-16፤ 35:7፤* የእንስሳት ዕድገት የመሬት ለምነትና ለውጥ ምክንያት ይጨምራል *ኢሳ.35:1-2፤ አሞጽ.4:13፤ ኢሳ.11:6-9፤ 65:25*

6. *ጽድቅ፡* - ከዚህ መንግሥት ባህሪያት አንዱ ሲሆን በአጠቃላይ የእምነትን ወይም የሃይማኖትን ቅድስናና ጽድቅ ለሰዎች መመለስ ነው፡፡ የዚህ መንግሥት ገዥ ንጉሥም ካህንም ነው *መዝ.110፤* የመንግሥቱ ማዕከላዊ መቀመጫ ኢየሩሳሌም ነው *ሕዝ.37:27፤* እስራኤላውያን በመሪነትና በአስተማሪነት ይሳተፋሉ *ኢሳ.61:6* እግዚአብሔር (ያህዌ) በዓለም አቀፍ ደረጃ ይመለካል *ኢሳ.66:23* ይህም እውነተኛ አምልኮ ተግባራዊና የተለመደ ይሆናል *ዘካ:14:16-19*





## ክፍል ሃያ ስምንት

# የመጨረሻው መጨረሻ

### 28.1 የመጨረሻው ፍርድ ጊዜና ሁኔታ

መጽሐፍ ቅዱስ የተፈጥሮንና የፍጥረታትን ጅማሬና ፍፃሜ ይናገራል፡፡ የፍጥረት ጅማሬ እንደመገለጹ ሁሉ ፍፃሜውም እንዴት እንደሆነ አቅጣጫ ያሳያል፡፡

የመጨረሻው ፍርድ የሚከናወነው ከሺህ ዓመት መንግሥት (millennium) እና ከብዙ ትርምስ በኋላ ነው፡፡ ዮሐንስ ስለ ሺህ ዓመት መንግሥት ሁኔታ ሰይጣን ለሺህ ዓመት ሲታሰር በምድር ላይ ሰላምና ፀጥታ እንደሚሰፍንና በሺህ ዓመት መጨረሻ ሰይጣን ለጥቂት ጊዜ ከእስር እንደሚለቀቅ አሕዛብን በማታለል ጦርነት እንደሚያስከትት ያሳየናል፡፡ *ራዕይ.20:7-8፤* ነገር ግን ጦርነቱ በክርስቶስ አሸናፊነት ሲጠናቀቅ ወዲያው የመጨረሻው የነጭ ዙፋን ፍርድ እንደሚከናወን ቃሉ ይገልፃል፡፡ *ራዕይ.20:9-10*

### 28.2 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት

#### እርግጠኝነት

በመጨረሻ ዘመን ከሚከናወኑት ሁኔታዎች መካከል ትኩረት የሚሰጥበትና ዋናውን ስፍራ የሚይዘው የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት (መምጣት) ነው፡፡

## ክፍል ሃያ ዘጠኝ

# በመላዕክት ላይ የሚፈረድ ፍርድ

## 29.1 የመላዕክት ሁለንተናዊ ይዘትና አገልግሎት

መላዕክት መንፈሳዊ አካል ያላቸው ፍጥረታት ሲሆኑ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እነርሱም ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው እውቀት፣ ስሜትና ፍቃድ አላቸው፤ አካላዊ አቋማቸው የማይሞት ሆኖ ጋብቻን የማይፈፅሙና የማይወልዱ የማይዋለዱ እንደሆነ ተገልጿል። መላዕክት ከሰው የላቀ ኃይል እንዳላቸው ቢታወቅም በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የመገኘት መለኮታዊ ባህሪይ የላቸውም። መላዕክት የተለያየ ሥልጣንና ባህሪይ ቢኖራቸውም ሙሉ እውቀትና ችሎታ የላቸውም።

መላዕክት በሁለት ይከፈላሉ እነርሱም የብርሃን መላዕክትና የጨለማው መላዕክት ተብለዋል። የብርሃን መላዕክት መልዕክቶችን ከእግዚአብሔር ወደ ሰው እንዲያደርሱ ሲታዘዙ የሚያደርሱ፤ እግዚአብሔርን ለማገልገል ለማምለክና ለማክበር በታማኝነት ዘወትር ዝግጁ የሆኑ ናቸው። *ዕብ.1:6፤14 ራዕ.5:11-12 መዝ.148:1-2*

ስለዚህ የብርሃን መላዕክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው እንጂ ከሰው ወደ እግዚአብሔር መልዕክትን አያደርሱም እነርሱ ፍጡራን እንጂ ሊመለኩ ወይም ሊሰገድላቸው የሚገባ መለኮትነት የላቸውም። ስለሆነም በስማቸው ጸሎት ሊደረግ ወይም እንደ አስታራቂ አማላጅ ሊቆጠሩ አይፈልጉም። ይህንን





ሥልጣን የፈለገው ሉሲፈር እግዚአብሔር ከሰጠው የክብር ስፍራ የተጣለውም ያለቦታው ራሱን ከፍ ከፍ በማድረጉ ነው። አንዳንድ ሰዎች የቃሉ ዕውቀት በጥልቀት ስላልገባቸው ሌሎች ለራሳቸው ሥጋዊ ፍላጎት በሚያቀርቡላቸው የልጆች ጨዋታ የመሰለ ተረት ተረት ይዘው መላዕክት ያማልዱናል የሚሉ አይጠፉም። ይሁን እንጂ የብርሃን መላዕክትንና የቅዱሳንን ስም ይዘው ሕዝቡን በጨለማ ያስቀመጡና ለፍርድ እያዘጋጁ የሚገኙ የብርሃን መላዕክት ነን የሚሉ የጨለማ ሠራዊት ናቸው። የብርሃን መልዓክ የሆነው መልዓኩ ገብርኤል እንኳን ሐዋርያው ዮሐንስ በእግሩ ፊት ሊሰግድለት ሲወድቅ ‹‹እንዳታደርገው ተጠንቀቅ›› ብሎታል። *‹‹ይህንም ያየሁት የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ። በሰማሁትና ባየሁት ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልዓኩ እግር ፊት እንሰግድ ዘንድ ተደፋሁ። እርሱም እዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህ መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ›› (ራዕ.21:8-9)*

## 29.2 የጨለማው መላዕክት የመጨረሻ ፍርድ

የሰይጣን (የጨለማ መላዕክት) ሥራ ዘወትር የእግዚአብሔር ሥራ ተቃራኒና ዕንቃፋት መሆን ሰዎችንም ከእግዚአብሔር መንገድ ማውጣትና አመፀኞችና ክፉዎች እንዲሆኑ በማድረግ እርሱን በተለያየ መልክ እንዲያመልኩ ማባበል (ማታለል) ነው። በተጨማሪም ከፍ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው የክርስቶስ ተቃዋሚ ስም ወይም የስሙ ቁጥር 666 ያለበትን ምልክት በክንዳቸው ወይም በግንባራቸው እንዲቀበሉ ያደርጋል። *ራዕይ.13:16-17፤* በሺህ ዓመት መንግሥት ሰዎችን እንዳያስት የታሰረውና የተዘጋበት ሰይጣን በሺሁ ዓመት ማለቂያ ለጥቂት ጊዜ ይፈታና ጎግና ማጎግ የተሰኙትን የጦር ሠራዊቶች በቅዱሳን ሰፈርና በተወደደች ከተማ እንዲከፈቱ

የመጨረሻው ፍርድ ትምህርት እያንዳንዳችን ምንግዜም ተዘጋጅተን እንድንኖር የሚያደርግ ራሳችንን የምናይበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ በተጨማሪም እኛም ከእግዚአብሔር በነጻ ይቅርታ እንደተቀበልን ለበደሉን በነጻ ይቅርታ መስጠትን የምንማርበት ነው፡፡ እዚህ ላይ ልንገነዘብ የሚገባን በሌሎች ላይ ቂምና በቀል መያዝ እንደሌለብን ቃሉ ይነግረናል፡፡*‹‹ተውዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፏልና፡፡ ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማም አጠጣው ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ››ሮሜ.12፡19-21*

ከዚሁ ጋር ሰዎች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ቢበድሉ ለመበቀል ወይም ቅጣት እንዲያገኛቸው መመኘት አስፈላጊ አይደለም፡፡ *‹‹...እርሱም ኃጢአት አላደረገም፤ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤ መከራንም ሲቀበል አልዛተም...›› 1ጴጥ.2፡22-23፤* ጌታን በሰቀሉት ጊዜ *‹‹አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው›› አለ ሉቃ.23፡34፤* እስጢፋኖስም በተወገረና በሞተ ጊዜ ኢየሱስ ሲሰቀል እንደጸለየው *‹‹ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ›› የሐዋ.7፡60፤* እስጢፋኖስ በጭንቅና በመከራ ውስጥ ሆኖ እየሞተ ለገዳዮቹና ለአስጨናቂዎቹ መቅሰፍትን ሳይሆን ምህረትን ጠየቀ፡፡ ጳውሎስ የተባለው ሳውል እስጢፋኖስ እንዲገደል ከተባበሩትና ከአስተባበሩት ሰዎች መካከል አንዱ ሆኖ የሐሰት ምስክሮችን ልብስ ይጠብቅ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ነገሩ ባይገባውና ባይረዳውም የውስጥ ቅንዓቱ ለእግዚአብሔር የተቆረቆረ መስሎት እንደሆነ ያውቅ ስለነበር ጌታ ሲጠራው ይህ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው የተወለደው በእስጢፋኖስ የፀሎት ምጥ እንደሆነ እንገነዘባለን ስለዚህ የመጨራሻው ፍርድ ትምህርት የክርስቶስ ኢየሱስና የእስጢፋኖስ ምሳሌነት በመከተል ለሌሎች ምህረትን እንድንለምንላቸው ይገልጽልናል፡፡





የመጨረሻው ፍርድ ትምህርት ለቅዱሳን ኑሮ እንድንነሣሣ፣ የዘላለምን መንግሥትና የክብር ሽልማት እንድናስብ ያደርጋል፡፡ *ማቴ.6፡20*

የማያምኑና የመጨረሻውን ፍርድ የሚክዱ ሰዎችም እንዳሉ የታወቀ ነው፡፡ ስለ እነዚህ ሰዎች በመጨረሻም ዘመን እንደራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባቾች በመዘበት እንደመጡ ይህን እወቅ፡፡ እነርሱም የመምጣቱ ተስፋ ወዴት ነው? አባቶች ከሞቱበት ጊዜ ከፍጥረት መጀመሪያ ይዞ ሁሉ እንዳለ ይኖራል ይላሉ፡፡ *2ጴጥ.3፡3-4፤ ‹‹ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ፤ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ እርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮ መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል›› 2ጢሞ.3፡1-5*

እስካሁን በተለያየ ምክንያት ራሳቸውን ለክርስቶስ ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሰጥተው በእርሱ ያላመኑ ሰዎች መጽሐፉ እንደሚል በአስቸኳይ ንቅተው ወደ እምነት ካልተመለሱና ኃጢአት መሥራትን ካላቆሙ የመጨረሻው ፍርድ ያገኛቸዋል፡፡ *‹‹ጌታችሁ በምን ሰዓት እንደሚመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ!››ማቴ.24፡42*

አማኞችም ቢሆኑ በኑሮ በባህል በይሉኝታና በሰይጣን ውጊያ እውነተኛውን አምልኮ ችላ ብለው ከሆነ ራሳቸውን የሚመረምሩበት የዝግጅት ወቅት መሆኑን መረዳት ተገቢ ይሆናል፡፡ *‹‹ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና›› ማቴ.24-44፤ ‹‹ተመለሱ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ ስለምንስ ትሞታላችሁ?›› ሕዝ.33-11፤* እግዚአብሔር ማንም እንዲጠፋ ስለማይፈልግ ለንስሐና ለመመለስ ዘመንና ጊዜ ሰጥቷል *2ጴጥ.3፡9፤* ሰዎች ዛሬ በሥጋ እያሉ የሚወስኑት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውሳኔ ለነገው የዘላለም መኖሪያ ቦታቸው ወሳኝ ነው፡፡ *ሮሜ.6፡23*

## ክፍል ሠላሳ

# አዲስ አማይና አዲስ ምድር

## 30.1 የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን

ከመጨረሻው ፍርድ በኂላ አማኞች ለዘላለም ሙሉ ደስታና ሰላም ወዳለበት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባሉ። ኢየሱስም እንዲህ አለ *‹‹...እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ›› ማቴ.25:34፤* የምንገባበት ከዘላለም የተዘጋጀ መርገም ከቶ የሌለበት የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን የሚገኝበት ነው *ራዕይ.22:30*

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት እንደሚያስረዳው እግዚአብሔር ብሩካን ለተባሉት ልጆቹ ያዘጋጀው የዘላለም ሀገር እንዳለ ቃሉ የሚገልጽ ሲሆን ይህም ስፍራ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ተብሎ ይታወቃል። *‹‹አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርም አየሁ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና ባህርም ወደፊት የለም›› ዮሐ.21:1፤* በኢሳያስ መጽሐፍ ደግሞ *‹‹እኔ የምሠራቸው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ከፊቴ ጸንተው እንደሚኖሩ እንዲሁ...›› ኢሳ.66:22፤* ጴጥሮስም ደግሞ ስለተስፋ ቃሉ ተፈጻሚነት ሲናገር *‹‹...ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደቃሉ እንጠባቃለን›› 2ጴጥ.3:13፤* ይላል። ዮሐንስ በራዕዩ በመቀጠል *‹‹ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ እየሩሳሌም ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ›› ራዕይ.21:2፤* በመቀጠልም *‹‹ታላቅ ድምጽ ከሰማይ፡ - እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው። ከእነርሱም ጋር ያድራል እነርሱም ሕዝብ ይሆናሉ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል። እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው*





*ያብሳል ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ሃዘንም ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም የቀደመው ሥርዓት አልፏልና ብሎ ሲጮህ ሰማሁ›› ራዕይ.21:3-4*

ስለዚህ ከዚህ ክፍል የምንረዳው የዘላለም መኖሪያችን እግዚአብሔር ራሱ መሆኑንና የቀደመው የምድር ሥርዓት ጨርሶ ማለፉን ሲሆን ይህም ቦታ የእግዚአብሔር መገኛ መንግሥተ ሰማያት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልፃል። *‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ያላል ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት...›› ኢሳ.66:1፤* ኢየሱስም ለደቀመዛሙርቱ ስለ ጸሎት ሲያስተምር *‹‹...በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ...›› ማቴ.6:9፤* ብላችሁ ጸልዩ አለ። በጴጥሮስ መልዕክት ደግሞ *‹‹...እርሱም መላዕክትና ሥልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኂላ ወደ ሰማይ ሄደ በእግዚአብሔር ቀኝ ነው›› 1ጴጥ.3:22፤* መንግሥተ ሰማያት እግዚአብሔር በታላቅ ግርማው የሚገኝበት የተባረከ ሥፍራ ነው። በእርግጥ እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ በአንድ ጊዜ የሚገኝ (omni present) አምላክ ሲሆን እርሱ እንደፍጡር በተወሰነ ቦታ ብቻ ተወስኖ የሚገኝ ነው ብለን መገመት የለብንም። ነገር ግን መንግሥተ ሰማያት እልፍ አእላፋት መላዕክት የሰማያት ሠራዊትና የዳኑ ቅዱሳን ስለ ታላቅነቱ ክብር እየሰጡ ለእግዚአብሔር የሚሰግዱበትና የሚያመልኩበት ቦታ ነው።

መንግሥተ ሰማያት ሀሳብ ሳይሆን ትክክለኛ የእግዚአብሔር መገኛ ቦታ ነው። ሰዎች ሊረዱ የማይችሉት ከሥጋዊ አዕምሮና ከምድራዊ ሀሳብ ጋር አገናኝተው ሲሞክሩ ስለሆነ አቅጣጫ ይስታሉ።

## 30.2 የትንሳኤ አካል

አዲስ ኪዳን ስለመንግሥተ ሰማይ በተለያዩ መንዶች ሲገልጽ እንመለከታለን። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደሰማይ ባረገ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናውም ተቀበለውና ከአያናቸው ዕይታ ርቆ ሄደ ተለያቸውም *ሉቃ.24:5፤ ሐዋ.1:9* *‹‹...ይህ ከእናንተ ወደሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው›› ሐዋ.1:11፤* እስጢፋኖስ በሰማዕትነት ሲገደልም የቀደመው ሃይማኖት መሪዎች ካህናትና የህዝብ ሽማግሌዎች በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል ሲያደርጉ መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በሰማይ ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ ነበር ያየው። *‹‹...መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሄርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሄር ቀኝ ቆሞ አየና እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሄር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ›› ሐዋ.7:55-56፤* እስጢፋኖስ ያየው ቅዠት ሳይሆን እግዚአብሔር መንፈሳዊ ዓይኑ ተከፍቶለት በመንግሥተ ሰማያትም ኢየሱስን በሚገባ እንዳየው ተገልጾአል። ኢየሱስ ዳግም የሚመለሰው በማይደክምና ልዩ በሆነ በትንሳኤ አካል ነው።

ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጀሁላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ። *ዮሐ.14:2-3፤* ጌታ ኢየሱስ እኔ እሄዳለሁ መጥቼም እኔ ወዳለሁበት እወስዳችኋለሁ የሚለው የታወቀ ቦታ እንጂ ያልተጨበጠ ቦታ አይደለም።





## 30.3 የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ እና የጊዜ ገደብ የሌለው ዘላለም

ከታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ በኋላ በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር ላይ ዘላለም ይጀምራል።

**የዘላለሙ ባህርያት**

- በጉ ራሱ (ጌታ ኢየሱስ) ብርሃንዋ ነውና በአዲሱ ሰማይ ላይ ፀሐይና ጨረቃ አይኖሩም *ራዕይ.21:23*
- በአዲሱ ምድር ላይ ባህር የለም *ራዕይ.20:1*
- የቀደመው ሥርዓት ባህርያት የነበሩት ሞት፣ ሀዘን፣ ጩኸት፣ ስቃይ አይኖርም *ራዕይ.21:4*
- እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ከህዝቡ ጋር ይኖራል *ራዕይ.21:3*
- እግዚአብሔር ሁሉን አዲስ ያደርጋል *ራዕይ.21:5*
- በጉ ራሱ መቅደስዋ ነውና ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም መቅደስ አይኖራትም *ራዕይ.21:22*
- ቅዱሳን እግዚአብሔርን ያመልካሉ፣ ያመሰግናሉ፣ ይዘምራሉ *ራዕይ.4:9-11፤5:8-14፤7:9-12*

በዚህ የዘላለም ህይወት በሐሴት የሚኖሩት እስከ ሺው ዓመት ፍጻሜ ድረስ በምድር ላይ የኖሩ በጌታ ያመኑ ቅዱሳን ሁሉ ናቸው፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ያላመኑት ግን የዘላለም መኖሪያቸው የእሳት ባህር ይሆናል። *ማቴ.25:41፤ ራዕይ.20:12*

***‹‹ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም››***

*ማቴ.24:35*

## ዋቢ መጻሕፍት

1. *አርማጌዶን* በዶክተር ጆን ኤፍ ዋልቮርድ በሰለሞን ደረጀ የተተረጎመ 1988 ዓ.ም
2. *ሀሳበ ዘመንና ታሪኩ* በአለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ 1981 ዓ.ም
3. *አጭር የታሪክና የሃይማኖት ሥርዓት መጽሐፍ* በትንሳኤው ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1975 ዓ.ም
4. *ኢትዮጲስ አንደኛው* በግርማ ዘውዴ በት.መ.ማ.ማ.ድ 1985 ዓ.ም
5. *ኢትዮጲስ ሁለተኛው* በግርማ ዘውዴ በንግድ ማተሚያ 1992 ዓ.ም
6. *ምልክቱ* በፒተር የንግሪን ብራና ማተሚያ 1993 ዓ.ም.
7. *መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት* በሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን
8. *የኢትዮጵያ ሥልጣኔ* ከበላይ ግደይ 1983 ዓ.ም.
9. *systematic theology* Wayne grudem, 1994
10. *contemporary obtains in Eschatology* Millard J.Erickson
11. *Anti Christ vol.1* L. R. Shelton D. D
12. *The hand book of ancient and medieval history of Ethiopia up to 1855*
13. *New Testament Survey A Study Guide fifth edition* Jesse K. Moon

*ስለመጽሐፉ ጥያቄ ወይም አስተያየት ካለዎት*
*በፖስታ ሳጥን ቁጥር 26718*
*አዲስ አበባ ብለው ይጻፉልን።*